ወርሀዊ

# ቅንዲል

DIGITAL MAGAZINE ቅፅ-1 ቁጥር-4
ግንቦት 2011



"....መሪነት ጥበብ ፣ ጥበብ ደግሞ ለእኔ
እንደ ጥልቅ ባህር ነው!..."

ወ/ሮ ፍፁም ኪዳነ ማሪያም

**#አጃኢብ**
የ30አመቱ ሽማግሌ

**#አዕምሮ ጤና**
በስሜት መለዋወጥ ተሰቃየሁ!

**#ሀገሬ**
ቁስልሽ የሚያመው ያ ትውልድ

# ማውጫ






## 3-4 ሀገሬ
ቁስልሽ የሚያመው ያ ትውልድ!
( በሀይሉ ወንድይፍራው )

## 5-7 አብርሆት
አስቦ መወሰንና ወስኖ ማሰብ ልዩነቱ ምንድን ነው?
( በ ታምራት ታደሰ )

## 8 ትዝብት
ሞትን አለማመዳችሁን
( በ ዳዊት ላቀው )

## 9-13 የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከ ወ/ሮ ፍፁም ኪዳነማሪያም ጋር

## 14 ጥበባት
ጥቁር ምስል (ክፍል2)
( በ ሳኦል አክሊሉ )

## 17-18 አጃኢብ
የ30 አመቱ ሽማግሌ
( በ ያብስራ ካሳ )

## 19-20 አዕምሮ ጤና
በስሜት መለዋወጥ ተቸገርኩ!
( በ ፍራኦል መስፍን )

## 21 ስነ-ፈለክ
አስትሮሎጂ
( በ ዞስ ካለስ )

## 23-24 ቅምሻ
ጥላ
( በ ሎዛ አድማሱ )

## 26-27 እልፍ ገፆች
ሊያነቧቸው የሚገቧቸው 4 መፅሀፍቶች
( በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ )

## 28 ቴክኖሎጂ
ሀሳብን ወደ ድምፅ እና ፁህፍ መቀየር የሚያስችል የቴክኖሎጂ ውጤት ይፋ ሆነ!
( በ ዞስ ካለስ )



ቅንድል
KENDEL
DIGITAL MAGAZINE

# የአዘጋጁ መልዕክት

ውድ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ተከታታዮች ከእናንተ ከአንባቢያን የደረሰንን የተለያዩ ሀሳብ እና አስተያየቶች ተቀብለን መፅሔታችንን በአዲስ እና በልዩ አቀራረብ ለማቅረብ ዝግጅታችንን አጠናቀናል። ከዚህም ውስጥ የስም እና የሎጎ ለውጥ፡ የይዘት እና አቀራረብ እንዲሁም ወደ እናንተ የምንደርስበትን መንገዶች ጥራት እና ብዛት ጨምረን እነሆ ለእናንተ ለአንባቢያን እንካችሁ ብለናል።

**የመፅሔቱ ስያሜ**

የመፅሔቱ ስያሜ እራሳቸውን ችለው ትርጉም ከሚሰጡ ሁለት የተለያዩ ቃላት በጥምረት ሰፊና ጥልቅ ትርጉም እንዲይዝ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ይህውም "ቅን" እና "ድል" ከሚሉ ሁለት ቃላት ቅንጅት "ቅንድል" የሚል ጥምር ቃል እንዲሰሩ ሆነው የተመሰረቱ ናቸው።

**የስሙ ትርጓሜ**

"ቅን" የሚለው ቃል በጎ፡መልካም፡ ጥሩ የሚል ተቀራራቢ ፍቺ ሲኖረው "ድል" የሚለው ደግሞ ማሸነፍ፡ መርታት፡ ማንበርከክ የሚል ፍቺዎችን ይይዛል። ታድያ እነዚህን በፍቺ የሚለያዩ ሁለት ቃላትን በማጣመር "ቅንድል" የሚል አንድ ጥምር ቃል ይሰጠናል ይህውም "ቅን" ሰርተን፡ "ቅን" አውርተን፡ "ቅን" አስበን ተንኮልን፡ ጥላቻን፡ መጥፎነትን፡ አለማወቅን "ድል" እናደርጋለን የሚል ነው።

**የመፅሔቱ ዐላማ**

ይህች መፅሔት በዋነኝነት ዓላማዋ አድርጋ የተነሳችው በመላው የሀገራችን ኢትዮጲያ የሚገኙ ወጣቶች ባላቸው እውቀት ፣ ክህሎት እና ችሎታ ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ የአነቃቂ እና የሚያንፁ ፅሁፎችን ለአንባቢያን ማድረስ፣ በመላው ሀገራችን ያሉ ወጣቶች የቅንነት እና ሀገር ወዳድነትን ፣ ምክንያታዊነትን እና የአንድነት አመለካከቶችን ማዳበር ብሎም ከታላላቆቻቸው እና በሙያቸው ለሀገራችን ብዙ ስራ የሰሩ ባለሙያዎችን ልምድ የሚካፈሉበትን መድረክ ማመቻቸት ነው።

ለእያንዳዱ ተግባር መነሻው ሀሳብ ነው። ቅን(መልካም) ሀሳብ እልያም አስተሳሰብ ደግሞ ፍሬው ያማረ እና ጣፋጭ ነው። በዚህም ወጣቶች (ተማሪዎች) በየትኛውም መጥፎ አጋጣሚ ላይ ቢሆኑ ቅን አስተሳሰብን በማዳበር መልካም ነገሮችን መስራት እንደሚችሉ ሊረዱ የሚችሉበት፡ ለእያንዳንዳቸው እንቅስቃስያቸው እና ድርጊታቸው ምክንያታዊነትን የሚለማመዱበት፡ ሀገራቸውን ይበልጥ የሚረዱበት እና የሚወዱበት ጽሁፎች የሚቀርብበት መፅሔት ነው።

ቸር ያቆየን!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይባርክ!
ኤርሚያስ ደጀኔ


ዋና አዘጋጅ፡-ኤርሚያስ ደጀኔ
0912178520
Email-
ErmiyasDejene@gmail.com
Telegram-@Jeremy00

አዘጋጅ፡-ሀና ሀይሉ
0935965345
Email-HanaHailu016@gmail.com
Telegram-@HanaHailueth

አርታኢ፡-አወት ሀይለስላሴ
0920152581
Email-Awoth12@gmail.com
Telegram-@Awicha12

አርት ዳይሬክተር ፡-ፍራኦል መስፍን
0923602445
Email-firaolmesfin8@gmail.com

መፅሔት ዲዛይንእና ግራፊክስ፡-እስራኤል
0920019699
Email-Esrumh1@gmail.com
Telegram-@Esrumh

በሀይሉ ወንድይፍራው
( መባ ጥቁር ሰው )
( ethiomebreku3000@gmail.com )



# ቁስልሽ
## የሚያመው ያ ትውልድ!

*ትውልድ......*
*እንኳን ለባንዲራ*
*እንኳንስ ለሀገር*
*ለትልቁ ነገር*
*በወዳጅ ተጣልቶ ይፋጃል ባላገር*
*ያ ትውልድ ታላቅ ነው ፤ ቁስልሽ የሚሰማው*
*ትናንቱን ለግሶሽ በማይናድ ታሪክ ዛሬሽን የሰራው።*

ዘመን በትውልድ ቅብብል የተሰራ ሰንሰለት ሆኖ በየግዜው ያሉ ሁሉ ይብዛም ይነስም፣ ጥሩም ይሁን መጥፎ ብቻ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ታሪክ ጽፈው ያልፋሉ። በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ እሳት ነዶ የትውልድ እንጀራ ያበሰለ፣ የድንበር ግንቧን በደሙ አብኩቶ የገነባ፣ ነጻነቷን ያቆየ፣ ቁስልሽ ህመመሜ ብሎ የሀገርን ህመም ህመሙ አድርጎ ተቀብሎ ያ ትውልድ ትናንት በመከራ እና በእሳት ተፈትነው ዛሬን በክብር የሰጡን እልፎች ናቸው ።

ያ ትውልድ ከእኔ ይልቅ እኛ የሚል ታላቅ መንፈስ ያለው፣ ስለሚቀይረው ሰው ሰራሽ ጨርቅ ሳይሆን ህልሙን ስለሚኖርባት፣ ማንነቱን የቀዳባት የህልውና ምንጩ ከሆነችው አጥታ ከማተዋት፣ ንደዋት ከማትፈርሰው በእሳት ከተፈተነችው ሀገሩ ለደቂቃም ቢሆን አይደራደርም።
ሰላም ሰላም !!! ውድ የቅንድል መፅሄት አንባቢያን ወሩ በብዙ ትሩፋቶች ታጅባችሁ ያሳለፋችሁት እንደነበር እምነቴ ነው። ዛሬ በሀገሬ ዐምድ ገበታ ለዛሬ እኛነታችን ትናትናቸውን ለሰጡን አቀርቅረን ከመሄድ አንገታችንን ቀና እንድናደርግ መስዋዕት የሆኑትን ታሪክ ሰሪ ትውልዶች ለመዘከር ወደድኩ።

ለዚህ ትልቅ ምክንያት የሆነኝ ባሳለፍነው ሚያዚያ 27 ለ78ተኛ ግዜ የተከበረው የጀግኖች አርበኞች የድል በዓል ነው። አርበኝነት የሀገር ቁስል ሲሰማህ፣ ክብርህን ስትሻ፣ ከሰው እና ከሀገር በላይ ሆነህ ለመኖር ሳይሆን ከሰው እና ከሀገር በታች ሲያዩህ አንተ የራስህ መገለጫ ያለህ ባለ ሀገር እንደሆንክ የምታስመሰክርበት የእውነት፣ የአሸናፊነት፣ የጀግንነት፣ የአልደፈር ባይነት ፣ የአላማ ጽናት፣ የሀገር ፍቅር እና የመስዋዕትነት ካባ ነው። ሀገራችን ኢትዮጲያ በተለያዩ የዘመን አውዶች ታሪክ በወርቃማ ብዕር የጻፋቸው ትንድ ትውልዶች ነበሯት።

ከነዚህም ወርቃማ ትውልዶች መሀል በ 1928 ዓ.ም ጣሊያን ኢትዮጲያን ዳግመኛ በመውረር የአድዋ ድልን በበቀል ለማስፈፀም ስትጀምር ከድሎት እና ምቾት በላይ የሀገር ቁስል ተሰምቷተቸው በህወታቸው ተማምለው ሀገራቸውን ሀገርን ነጻ ለማውጣት ብዕር ጽፎ የማይጨርሰው መስዋትነት የከፈሉ እልፍ ጀግኖች ነበሯት። ያ ትውልድ የሀገር መንፈስን እንጂ ዘመን እንዳመጣሹ የኔ ዘር በሽታ የተደቆሱ አልነበሩም። ቋንቋ ልዩነቱ እንደ ሀገሩ ታሪክ የውበት እና ጀግንነታቸው መሞሸሪያ እንጂ የልዩነት መስመር አልነበረም።

ያ ትውልድ መገለጫው ድል ፣ ጀግንነት እና ሀገር ፍቅር ነው ፡ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን የሀገሩ ነጻነት የሱ የማንነት መሆኑ የገባው ታለቅ ትውልድ ነበር። ዛሬያቸውን ሳይሆን ነጋቸውን ያዩ ለዛሬ ማንነታችን በደም እና ባጥንታቸው ድልድይ የገነቡ፣ በክብር ተሞሽረው በማይጠፋ ቀለም በታሪክ ማማ የነገሱ አርበኞች ናቸው። በጅ የያዙት ወርቅ... ይባላል እና ከነ ሙሉ ነጻነቷ የተቀበልናትን ሀገር ከነ ክብሯና አንድነቷ ታሪክ ማስቀረት የኛ የዚህ ዘመን ትውልዶች የቤት ስራ ነው።

ጀግና ታሪከ ባይሰራ ታሪክ ያቆያል በርግጥ ባለንበት ዘመን ጠመንጃ አንግቶ የሀገር ነጻነት የሚጋፋ ጠላት ሳይሆን በስሜት ተመርቶ ሀገር የሚንድ ጠላት ነው ያለን። አዎ አሁን የኛ አርበኝነት ከአለማወቅ፣ ከድህነት፣ ከስሜት፣ ከዘር በሽታ እና እኔ ልቅደም ትርክት ነው መሆን ያለበት። አርበኛ ጠላት ገሎ የሚፎክር ብቻ ሳይሆን በአላማ፣ በእውቀት፣ በሀገር ፍቅር የቆመ የክቡር ሰው መጠሪያ ነው።
የተከበርከው የዚህ ዘመኔ ትውልድ ሆይ !!!
ለሞተልህ ያልቆምክ አንተ ለማን ልትሞት ነው?
ጥያቄው ለትውልዴ ነው
የዘመኔ ትውልድ ሆይ ኢትዮጲያዊነት ነጻነትና መስዋትነት ነው። ሀገር ነጻ አድርገህ አንተ ለዓላማህ የምትሰዋበት የከፍታ ማማ ልብ በሉ አንገታችን ቀና ያለው፣ ልባችን የኮራው ፣ ዛሬን የተሰጠነው፣ የምንረግጠው ምድር በሞቱልን ሰማዕትነት ነው።

ውድ የሀገሬ አምድ አንባብያን !! ለዛሬ ዕሁፌ መቋጫ ይሆነኝ ዘንድ እንዲሁም ለታላላቆቹ የሀገራችን ባለውለታ አርበኞች 78ተኛ የአርበኞች ድል ቀን ምክንያት በማድረግ አንድ ሴት እና አንድ ወንድ አባት አርበኞችን በመዘከር ነፍሱን ይማረው እና አንጋፋው የጥበብ ሰው የሙዚቃው ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ በህይወት እያለ ሰርቶት ለህዝብ ሳያደርሰው ካለፈው ሙዚቃው ጥቂት ስንኞች ጀባ በማለት በቅንድል አምስተኛ ዕትም በሌላ የሀገሬ ርዕስ እስከምንገናኝ እያንዳንዷ ቀን እና ሰዓት ለወገናችን አንድነት፣ፍቅር፣ስኬት የምንሰራበት እንዲሆን እየተመኘሁ።



ከጀግኖች አንባ

ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ

በስማቸውና በፆታቸው ሴት ናቸው ። በቆራጥነታቸውና በጀግንነታቸው ግን የወንድነት ስም የተሰጣቸው ዝነኛ አርበኛ ነበሩ ። ከፈፀሟቸው የጀብዱ ሞያዎች መካከል ፦ በወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ የኢጣልያ ሲሰቀል አልቅሰሻል ተብለው ተከሰው ከፋሽስት ከፍተኛ የጦር ሹማምንት ፊት ቀርበው ይጠየቃሉ ። ጀግናዋ ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ ግን በዚያን የግፍና የመከራ ሰዓት ፣ ሴትነታቸው ሳያግዳቸው ያለ አንዳች ፍርሀትና መርበትበት ቁርጥ ባለ አነጋገር ክሳቸውን ተቀብለው እንዲ አሉ ፣
<< አዎ አልቅሻለሁ ፤ የእናንተ አገር ሴቶች በሰው አገር ቀንተው የጣታቸውን ቀለበት እያወለቁ ኢትዮጵያን ለመውረር ለመጡት ሽፍቶች ሲያበረክቱ እኔ አገሬ በባዕድ ሕዝብ ሲወረር መንግሥት ጠፍቶ የአገሬ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ ሌላ ሲሰቀል ለሰንደቅ ዓላማዬ ማልቀስ ይነስብኝ ወይ ? >> ሲሉ መልሰዋል ።
ከዚህም በቀር ለአርበኞች ስንቅ ታቀብያለሽ ፣ ቀይ መስቀልን ትረጂያለሽ በሚል ተወንጅለው ለጥያቄ ቀርበው ነበር ። ወይዘሮዋ ግን አሁንም በክሱ ህሊናቸው ሳይሸበር " ስለ ነፃነት ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው የሌሊት ቁርና የቀን ሀሩር ከሚገርፋቸው የሀገሬ አርበኞች ጎን ተሰልፌ ጠላቴን መውጋቴ ቀርቶ የርሀብና የጥም መድሀኒት እያዘጋጀው መላኬ ቁምነገር ሆኖ ነው የተጠይቅሁበት ? እኔ ይህን ባላደርግና ለሀገርም ባልቀረቀር እንኳ እሱ እናንተም እንደምትታዘቡኝ ይሰማኛል" በማለት በጠላት ፊት ለሀገራቸው ፣ ለወገናቸውና ለባንዲራቸው ያላቸውን ፍቅር በልበ ሙሉነት ያስመሰከሩ ታላቅ ኢትዮጲያዊት ጀግና ነበሩ ።

ሌላኛው በዛሬው የሀገሬ ዐምድ ላይ የምንዘክረው ወጣቱ አርበኛ እና የሐገር አለኝታ አርበኛ ዘርዐይ ደረስ በመባል ይታወቃሉ።



**ዘርአይ ደረስ**

ጀግናው ዘርኢይ ደረስ በኤርትራ ክፍለ አገር ሐማሴን ውስጥ አዘጋ በምትባል መንደር በ1908 ዓ.ም ተወለደ ኢትዮጵያ በጣሊያን ፋሽስት ነፃነቷ ተደፍሮ በነበረበት ወቅት በግንቦት በ1937 ዓ.ም እ.ኢ.አ በኢጣሊያ ዋና ከተማ በነበረቺው ሮማ በአስተርጓሚነት ለመስራት ሄደ ። ዘርኢይ ደረስ ወደ ኢጣሊያ ለማቅናት ስበብ የሆነው ብዙ ኢትዮጵያውያን በእስረኝነት ወደ ኢጣሊያ ተወስደው ስለታሰሩ ጣሊያንኛ ስለማይችሉ እነሱን በአስተርጓሚነት ለመርዳት ነበር ። ዘራይ ደረስ ትግሪኛ፣አማርኛ፣ኢጣሊያ ቋንቋ አጣርቶ መናገር ይችል ነበር።

ሰኔ 7, 1938 ዓ.ም በሮም ፒያሳ ዲፒያሜንቴ በዶጋሊን ጦርነት ላለቁ 500 ኢጣሊያዊያን ለማሰብ ህዝቡ በአደባባዩ ተሰብሰቧል ዘርኢይ ደረስም ወደ አደባባዩ እንዲመጣ ጥሪ ተደርጎለት ነበር። ወጣቱ ዘራይ ደረስም ወደ አደባባዩ የራስ አሉላን አባ ነጋን በ1871 ዓ.ም በዶጋሊን ጦርነት ጀብዱ የፈፀሙበትን ጎራዴ ይዞ ወደ አደባባዩ ደረሰ በዛን ሰዐት የኢጣሊያ ወታደሮች በአሁኑ ወቅት አገራችን ላይ ተመልሶ ለገሀር የቆመው የይሁዳ አንበሳ ተብሎ የሚጠራውን ሀውልት ነቅለው ወስደው እየተዛበቱበትና የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማን እመሬት አንጥፈው ሲረማመዱበት ባየ ጊዜ ዘርኢይ ደረስ እጅግ በመቆጣትና ንዴት በተቀላቀለበት በኢትዮጵያዊ ወኔና አልደፈር ባይነት በያዘው ጎራዴ አፀፋውን ሰጣቸው።

ከዚያም በልበ ሙሉነት በእሁልቱና በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ፊት በሮም አደባባይ እንዲ ሲል ንግግሩን ቀጠለ ።
"እናንተ ኢጣሊያዎች ነፃነታቹን ካገኛቹ ገና ጥቂት ጊዜ ነው። ስለነፃነት አንዳችም ነገር ስለማታውቁ ነውራቹ እዚህ በምታደርጉት ተገልፆል" እያለ በቁጣ ንግግር እያደረገ እያለ ከእርቀት የቆመ የጣሊያን ወታደር ተኩሶ እግሩን በመምታት ይዞ ለፍርድ አቀረበው ።
ከዛም እብድ ነው በማለት አእምሮ ታማሚዎች ሆስፒታል ያስገቡታል ፤ ከዚያም በእስር ከቆየ በኃላ ኢትዮጵያ ዳግም ነፃነቷን አስጠብቃ ጣሊያንን ስታባረር ዘርኢይ ደረስም ወደ እናት አገሩ እንዲሄድ ውሳኔ ተሰጥቶት ሳለ ወደ አገሩ ኢትዮጵያ ሊመለስ በዝግጅት ላይ ሳለ በድንገት ህይወቱ አለፈ።
ይህ ጀግና ኢትዮጵያዊ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ በስሙ እንዲሰየምለት ተደርጓል ፤ በአዲስ አበባም ተክለሀይማኖት አካባቢ በስሙ ትምህርት ቤት ተሰይሞለታል ።
ምንጭ፡ ምንጭ ቀሪን ገረመው-ቀኝአዝማች ታደሰ ዘወልዴ ከመጽሀፍት አለም ገጽ
# ክብር አባት እና  እናት አርበኞች ሁሉ ይሁን !!

*ቆሜ ልመርቅሽ ተቀበይኝማ*
*ሂወቴን መርቀሽ ሰተሽኝ እኔማ*
*ይህ ቀረኝ የምለው የሚቆጨኝ ባለም*
*ኢትዮጲያ ዕድሜ ላንቺ ያላየሁት የለም*
*አንገትሽ እራስሽን ችሎ ልየው እና*
*ማግስቱን ይውሰደኝ 10ሞት ይምጣና*
*እማማ ካረግንልሽ በላይ*
*እማ የምታይልን*
*መጠሪያ እናታችን አንቺ ኑሪልን።*

ለሞተልህ ያልቆምክ አንተ ለማን ልትሞት ነው?
ኢትዮጲያዊነት ነጻነት ና መስዋትነት ነው።
አንገታችን ቀና ያለው፣ ልባንችን የኮራው ፣ ዛሬን የተሰጠነው በሞቱልን ሰማዕትነት ነው።
‹‹ መልካም እና ሰላማዊ ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይመለስ የለም ››
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር...



በ ታምራት ታደሰ
( addisayer@gmail.com )

# አስቦ መወሰንና ወስኖ ማሰብ

## ልዩነቱ ምንድነው?

### እነዚህ ሁለት ባህሪያት የምን መገለጫ ናቸው?

ከልጅነት እስከ ዕውቀት ባሳለፍኩባቸው አጭር የህይወት ዘመን ውስጥ ውሳኔ የሚያስፈልጋችው ጉዳዮች በብዛት አጋጥመዉኛል። አንዳንዶቹን አጎንብሼ በማለፍ ከኋላዬ እያየኋቸው እስከዛሬ የተከተሉኝ በግልፅ የማያቸውና ያኔውኑ በገባኝና በተረዳሁት መጠን ውሳኔ ሰጥቼ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ እስከዛሬ ድረስ እንደ አዲስ ባልተከተለኝና ባላስጨነቀኝ ነበር በማለት እቆጫለሁ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰው ጋር ለመመሳሰልና ሰዎችን ላለማስቀየም “መቻል ምን ይጎዳል ሆድ ከአገር ይሰፋል” በሚል ባህላዊ አባዜ ውስጤ ተጎድቶ ለሌሎች ስል የራሴን ደስታ ሰውቼ የኖርኩባቸው ጊዜያቶች ብዙ ናቸው።

አንዳንዴ ደግሞ አይቶ እንዳላዬ “ከሰው ሲኖሩ ሞኝ ሀኖ እህያ ሲጭኑ ሶስት ሆኖ” እንደሚባለው ስሜቴን የጎዱ ወስጤን ያሳመሙ ጉዳዮችን ዝም ብዬና ለማንም ምንም ሳልናገር በዝምታ የተውኳቸው ብዙ ናቸው። እነዚህ ብዛት ያላቸውና ውሳኔ ያልሰጠሁባቸው ጉዳዮች ውስጤን ያምስቱና ብቻዬን አወራለሁ አንዳንዴም ጮክ ብዬ ለራሴ እስኪሰማኝ ድረስ ሳወራ እደነግጥና ሰው አዬኝ አላዬኝ በማለትና በመሳቀቅ ቶሎ ወደ እንጉርጉሮ እለውጠዋለሁ። እንግዲህ ላለፈና ለሞተ ጉዳይ መፍትሔ ለመስጠት ሳወጣና ሳወርድ ሳስብ እውልና ምንም ለውጥ ሳልፈጥር በሃሳብ ጭልጥ ካልኩበት እባንናለሁ። ብቻ ይገርማል ይህ በኔ ህይወት ብቻ የሆነ አይመስለኝም ሌሎችም ቁጥራቸው ቀላል ባልሆኑ በኔ ዓይነት ባህልና አስተዳደግ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ህይወት ክስተት እንደሚሆን እገምታለሁ።

ዛሬ በጎልማሳ ዘመኔ ላይ ሆኜ ኋላዬን ሳስበው ደግሞ ምነው በአእምሮው የበሰለ አርቆ የሚያስተውል፣ ቁጭ ብዬ የማናግረውና የማወያዬው መካሪ ሰው ባገኝ ኖሮ ዛሬ በአእምሮዬ የሚመላለሱትን በወቅቱ ትክክለኛ መፍትሄ ያልሰጠኋቸውን ጉዳዮች በእንጥልጥል ባላስቀረኋቸው ነበር እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ልጆች ምንም አያውቁም፣ ዝም በሉ “በጨዋ አፍ ጨዉ አይሟሟም” እንደሚባለው ጨዋ ለመምሰል ያልሆንኩትን ለመሆን በልጅነት አቅሜ አስመስዬ ባህል የጣለብኝን ሸክም ያለዓቅሜ ተሸክሜ እንድኖር ሆኛለሁ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ለዛሬው ማንነቴ ወሳኝ ሆኖ እኔን እንደኔ ሳይሆን እንደ ህብረተሰቡ፣ ጥቂት ተደማጮች፣ ወላጅና ቤተሰብ እንደሚፈልገው የተሰራሁና የሌሎች ሃሳብ ውጤት ነኝ ብዬ እስባለሁ።

የሰው ልጅ በእያንዳንዱ ቀንና ሰዓት ውሳኔ ሳይወስን አይኖርም። ለምሳሌ ዛሬ ምን ሰርቼ ልዋል፣ የት መሄድ አለብኝ፣ በዚህ ሰዓት ምን ማድረግ አለብኝ፡ ለምሳ ምን እበላለሁ፡ በተሰማራበት መስክ በጦርነት ይሁን፣ በንግድ፣ በትምህርት ይሁን በሥራ፣ በሃይማኖት ይሁን በፖለቲካ፣ በትዳር ይሁን በገንዘብ በሁሉም ነገር ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ውስጥ በየዕለቱ ያልፋል። ሆኖም ግን ስንቶቻችን ነን በውሳኔያችን ደስተኛ ሆነን የምንኖር፣ ስንቶቻችን ነን ደግሞ የተፀፀትን፣ ስንቶቻችን ነን የትናንቱ ውሳኔያችንን ስናወጣ ስናወርድ ዛሬን የምናበላሽ ብቻ ቤቱ ይቁጠረው።

በዚህና ባለፈው ትውልድ ከምናያቸው ጥቂት ችግሮች ለምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ ስደት ከሄዱ በኋላ ምነው ያን ቀን እግሬን በሰበረው፣ አሁን ምን ይዤ ነው ወደ ሃገሬ የምገባው፣ ተመልሼስ ምን አደርጋለሁ በሚልና በተለያዩ ጥያቄዎች እራስን በማስጨነቅ ሁለት ልብ ሆኖ ዕድሜ መጨረስ፣ በትዳር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለምንድነው በቂ ዝግጅት ሳላደርግ ሌላ ሰው አይቼ ያገባሁት፣ ልጆቼንስ በምን ላሳድግ (ልጅ በዕቅድ እንጂ በዕድል እንደማይወለድና እንደማያድግ ካለመረዳት)፣ አበድሮ ከተበዳሪ ጋር በፍርድ ቤት መንከራተት፣ አባ ከተባሉ በኋላ ቆብን አውልቆ አግብቶ መውለድ፣ ሰውን የሚያህል ትልቅ ፍጡር ከገደልን በኋላ መፀፀት፣ ሌላ ሰው ተምሮ ውጤታማ የሆነበትን የትምህርት መስክ እኛም ተከትለን የተፈጥሮ ዝንባሌና ፍላጎቱ ሳይኖረን ውስጣችን እየጮኸ እያመመን ገንዘብና ጊዜያችንን አጥፍተን ትምህርቱን ከጨረስን በኋላ ውጤታማ ሥራ መሥራትና ዕርካታ ስናጣ ሌላ ትምህርት ደግሞ ሀ ብለን መጀመር፣ ይገርማል ሰው ሁሉ ማንነቱን ሳያገኝ ገንዘብና እራሱን ፍለጋ ትርምስና ሩጫ ላይ ያለ ይመስላል። በአጭሩ አቅጣጫ ጠፍቶብን ግራ በመጋባት እኛንና ዕድሜያችንን በማይመጠን የሃሳብ ትካዜና ምናብ ውስጥ ሆነን በምኞት ብቻ እንድንኖር ሆነናል።

እዚህ ላይ ሳልጠቅሰው የማላልፈው የአንድ አፍሪካዊ የሽምቅ ተዋጊ ሰው ታሪክ በአንድ መጸሐፍ ላይ እንደተጠቀሰውና እንዳነበብኩት የዘወትር ፀሎቱና ጥያቄው ፈጣሪ ሆይ ጠይቆ የመረዳትን ጥበብ ስጠኝ ነበር። ይህም ማለት የተሰማራበት የነፃነት ዉጊያ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑና ውሳኔ ለመስጠት መመርመር ማሰብና ማስተዋል እንደሚያስፈልግ በመረዳት እራሱን ከስህተት ለመጠበቅና በተሰማራበት የህይወት ጉዞ ውጤታማ እንዲሆን፣ በተከታዮቹ ፊት በሚሰራው ስህተት ላለመፈረጅና የቆመለት ዓላማ እንዳይጨናገፍ ሲል የራሱን የዓቅም ውስንነት በመረዳት ፈጣሪው እንዲረዳው ዘወትር ይፀልይ እንደነበር ያወሳል።

ይህ ሰው በምዕራቡ ዓለምም ብዙ አድናቆትን ያተረፈ ሲሆን ዋናው ምክንያት ግን በዕርጋታና በማስተወል አስቦ መወሰን የየዕለት ህይወቱ መርህ አድርጎ ይጠቀም ስለነበር ነው።

አበው "አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ ቀድሞ ነበር እንጂ ቀምሞ መደቆስ" እንደሚሉት ዕቅዶቻችንን በጥንቃቄ ሳናስተውል ሳንረዳውና ሳንዘጋጅ በስሜት እንጀምርና መሃል ላይ ስንደርስ እንቆማለን። ይህ ችግር በሃገራችን በሜጋ ፕሮጄክት የተለመደ የዘወትር ክሰተት ሲሆን በመንደር በሚሰሩ ትናንሽ ሥራዎች፣ በቢሮና በፍርደ ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቁ ጉዳዬች ሲጓተቱ ማየት፣ በቂ ሥራ መፍጠር ሳይቻል በብዙ ሺህ የሚቆጠር ተመራቂን ለሥራ ገበያ ማቅረብ የተለመደ ሲሆን ከሚቀርቡት ምክንያቶች ጥቂቶቹ ደግሞ የአቅም ውስንነት፣ የማቴሪያልና የውጪ ምንዛሬ ዕጥረት፣ በቂ ሥራ መፍጠር አለመቻል፣ የአየር ንብረት ሳይቀር ምክንያት ሆኖ ይቀርባል። የሚያሳዝነው ዝናብ እንደማይዘንብ ተደርጎ ይታቀድና ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ሲዘንብ ሥራውን ማስኬድ አልቻልንም ተብሎ ለሥራው መጓተት እንደምክንያት ይቀርባል፣ ዝናብ በወቅቱ እንደሚዘንብ አለማወቅ በሥራ ሰጪና ተቀባይ መሀል ያለው ትኩረት ሥራው ሳይሆን ሌላ ጉዳይ መሆን አለበት። ይህንና የመሳሰሉትን ክስተቶች ለማስተባበል ደግሞ በሺህ የሚቆጠር ምክንያት በማቅረብ ብዙ መጠየቅና መብቱን ማስከበር የማይችለውንና የማይመረምረውን ህብረተሰብ በጨለማ ማኖር የተለመደ ነው።

በምዕራቡ ዓለም ከመቶና ሁለት መቶ ዓመት በፊት በጥንቃቄ ታቅደው የተሰሩት ህንፃዎች ለከተሞቻቸዉ ዉበትና የቱሪስት መስህብ ሆነው ለማየት አጓጊ ሲሆኑ ዛሬም በዚህ ዘመን የሚሰሯቸው ህንፃዎች ካለው የአስተሳሰብና የቴክኖሎጂ ዕድገት ደረጃ ጋር ተጣጥመው ስለሚሰሩ በታሪክ ቅርስነት ለመጪው ትውልድ ማውረስ የተለመደ ነው።

በኛ በኩል ደግሞ ከመንገድ አቅም ተሰርቶ ይፈርሳል፣ የአግረኛ መንገድ በቴራዞ ከተሸፈነ በኋላ ጥቂት ሳቆይ ይቆፈርና የአፈር ክምር ሆኖ ለዓይነ ሥውርና ለአቅመ ደካማ የአደጋ መንስኤ ሆነው ይቀራሉ። ዉበታቸው ሳይሆን አስፈሪነታቸው ጎልቶ የሚታዩው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የከተማችን ህንፃዎች መንፈስን የሚረብሹ ዓይንን የሚያሳምሙ ከመሆናቸው የተነሳ ወደፊት ጥበብና ማስተዋል ታክሎባቸው ፈርሰዉ እንደ አዲስ ቢሰሩ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም የሚል የባለሙያ አስተያዬትም አለ።

እዚህ ላይ የሰው ልጅ ባህሪና ድርጊቱ እንደባለሙያዉ የዕዉቀት ደረጃ የተለያዬ ትንታኔ ቢሰጠውም በእኔ እይታ ግን ሞኝ፣ ብልጥና ብልህ ሊሆን ይችላል በዬ እገምታለሁ። ሞኝ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ስህተትን ይሳሳታል ቢመክሩትም አይሰማም፣ ብልጥ ግን ከስህተቱ በቶሎ ይማራል ተመሳሳይ ስህተትን ግን አይደግምም፣ ብልህና ጥበበኛ ሰው ግን ከሌሎች ስህተት ይማራል። እንግዲህ ከየትኛው እንደምንመደብ ባለውቅም የአንዱን ሥራ ሌላው እያፈረሰ ዘመናት አስቆጥረናል። ይህ ደግሞ በመንደርና በመንገድ ዳር ላይ ብቻ የሚቀር ክስተት ሳይሆን በአደባባይ በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥም በግዙፉ ይስተዋላል። ለምሳሌ የአንዱ የፖለቲካ ሥርዐት እራሱን ብቻ ለማቆየት የነደፈውን የመንግሥት ሥርዐት ሌላው አሽንፎ ሲመጣ በአዲስ ሥርዓት ይተካዋል። እንደታዛቢ ወይም ተመልካች ለእኔ እጅግ አሳዛኙና አስደንጋጭ የሆነው ጉዳይ ሃገራችን ወጥ የሆነ ሁሉም የተስማማበት መለያ ባንደራ እስካሁን እንደሌላትና ገና ለህዝብ ውይይትና ዉሳኔ እንደሚቀርብ ስሰማ ነው።

በዚህ ላይ በዙ ተመሳሳይ ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል ሆኖም ግን የኔ ትልቁ ትኩረት ችግሩ ለምን ተፈጠረ ሳይሆን ምክንያቱ ምንድን ነው ስህተቱስ የምን መገለጫ ነው የሚለው ጉዳይ ነው። ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ በውጪ (በአንደኛው ዓለም) ሃገር ስኖር ሰው እራሱንና የግል ህይወቱን በምን መልኩ ማራመድ እንደሚችል፣ ፣ ከፊቱ ባሉት ዓመታት የት እንደሚደርስና በምድር የሚኖርበትን ዕድሜ እንዴት ተጠቅሞበት እንደሚያልፍ እያሰበና ለህይወቱ ዕቅድ ሲያወጣ መንግሥት ደግሞ ከግለሰብ ለሚመጡ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ባለሙያ በማዘጋጀትና በተገቢው ሥፍራ በማሰቀመጥ እገዛ ሲያደርግ ህብረተሰቡ የዜግነት ሃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ሁኔታዎችን ሲያመቻች በተቃራኒው ደግሞ ሃገራችን ዜጎቿን የረሳች ይመስል ባለጉዳይ ሲጉላላ ህዝቧ ከኖረበት ሥፍራ ለቆ ሲሰደድ መንገዶቿ በጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ሲሞሉ ህዝብ በራሱ ሃገርና መሪዎች ሲያለቅስ የአእምሮ ብቃታችንና አስተሳሰባችን ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ እንደ ዜጋ እያንዳንዱ ሰዉ እራሱን በሃላፊነት መፈተሽ እንዳለበት ይሰማኛል።

ከላይ እንደጠቀስኩት የኔ ጥያቄ ለምን ይህ ሁኔታ ሆነ ሳይሆን በምን ምክንያት ሊሆን ቻለ ሲሆን የዚህ መልስ መገኛው ደግሞ በእርግጠኝነት በእያንዳንዳችን ልቦና ውስጥ ነው። ይህንንም ስንፈትሽ ትልቁን ድርሻ ይይዛል ተብሎ የሚገመተው በቅድሚያ የአእምሮ ዕድገት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፣ ከዕድሜያችን ጋር ያልተስተካከለ የአስተሳሰብ ዓቅም ክፍተት፣ በቂ መረጃ አለማግኘት፣ ሃሳብን በግልፅ አለመወያየትና ስህተትን መፍራት፣ ድብቅ የሆነና ግለፅነት የጎደለው የባህል ተፅዕኖ፣ ትክክለኛ አቅጣጫን የማያሳይ የግል የህይወት ዕቅድ አለመኖር፣ ለምናደርጋቸው ነገሮች በቂና አሳማኝ ምክንያትን ማፍለቅ አለመቻልና በራስ ያለመተማመን፣ ፍርሃትና ጥርጣሬ የበዛበት የቡድን ሰሜትን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት ከዚያም አልፎ ስለሃገራችንና ስለራሳችን ያለን የተሳሳተ ግምት ልምሳሌ ከዓለም በታሪክ፣ በባህል፣ በኢኮኖሚ አንደኛ፣ በትምህርት ከክፍል አንደኛ በሚል ሰው ሀገሩንና የራሱን ማንነት እንዳያውቅና እራሱን እንዲስት በሚደረግበት ማህበረሰብ ውስጥ ዝቅ ብሎ የራስን ችግር ማየት ማስተዋልና መፍትሄ ለመሻት መሞከር የማይታሰብ ነው።

ምክንያቱም ሰው ስለራሱ የተሳሳተ ግምት ካለው ይህንኑ ለማስተካከል የአንድ ወይም የሁለት ትውልድ ሥራን ይጠይቃል ያውም አቅጣጫው በትክክል ከተነደፈና ህዝብ በባለቤትነት ከተቀበለው፡፡

ከማንም በላይ ጠቢብ የሆነዉ ሰው “ጥበብ ትክክል መሆኗ በዉጤቷ ተረጋግጧል” በማለት በአንድ ወቅት ተናግሮ እንደነበር ሁሉ በአጭሩ የማሰባችን ጥልቀት የማስተዋላችንና የወሳኔያችን ትክክለኛነት ነፀብራቅ የሆነው የአእምሮአችን የዕድገት ደረጃና ማንነታችን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚህ ውሳኔያችን የማይፀናና ከጥቂት የጊዜ ቆይታ በኋላ ለፀፀትና ሰህተት የሚዳርገን ከሆነ፣ የጀመርነው ፕሮጄክት በታቀደው ጊዜና ዓብይ ዓላማ መሠረት የማይጠናቀቅና ዉጤታማ ካልሆነ፣ ለሃገር ውስጥ የብቃት ችግር ክህሎቱንና መፍትሔውን ከውጭ ሃገር ለማስመጣት የምንጥር ከሆነ ዕውነትም የአእምሮ የዕድገት ደረጃችን ዝቅተኛ መሆኑን ዕርግጠኛ መሆን አለብን፡፡ ይህው የአስተሳሰብ ችግር በሃገራችን እስከ ዛሬም ትኩረት ያልተሰጠውና ያልተሰራበት ትልቅ ጉዳይ ሲሆን የሰዎችን የህይወት ክህሎት ደረጃን ለማሻሻል ህዝብን ማሰልጠን አማራጭ የሌለው የመፍትሄ ዕርምጃ መሆኑን ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረዳት አለበት፡፡ ነገ እንዲሆን የምንፈልገውን ዛሬ መሥራት መጀመር አለብን፡፡ ከዚያም ከአስተሳሰብ ኋላቀርነት ነፃ ወጥተን ወስኖ ማሰብ ሳይሆን አስቦ መወሰን የህዝባችን ትክክለኛ መለያ ባህሪው ይሆናል፡፡ የዚህም ዉጤት ሃገራችን በአስተሳሰብ ልቀው ከሚገኙ የበለፀጉ ሃገሮች ተርታ ዕኩል የመሰለፏን ዕድል ሰፊ ያደርገዋል፡፡ የነበረንንም ትልቅነትና ክብር ከማንም ሳንጠይቅ አዋጅም ሳናውጅ በራሱ ጊዜና ሰዓት ከእጃችን እንደወጣ በእጃችን ተመልሶ እናገኘዋለን፡፡



#ትዝብት



በዳዊት ላቀው

# ሞትን

# አለማመዳችሁን

የቀን ውሎዬ እንደ አብዛኛው የኢትዮጲያ ህዝብ የታክሲ ወረፋ በመጀመር ይጀምራል ዛሬም እንደ አምናው ነው። የኑሮ ዘይቤ በርካታ የስነልቦና ባለሙያዎች የሰው ልጅ የራሱን ህየወቱ ደራሲ አድረገው ይስሉታል ለዚህም  እንደ ማሳመኛ ነጥብ ሚያነሱት የበርካታ ስኬታማ ሰዎችን የጥረት ውጤት እና ስኬታቸውን ነው። በነሱ አንድምታ ሰው ህይወቱን አዘቅት ውስጥም  ከአዘቅትም  የማውጣት እድሉ በጁ ነው በማለት ነው ። ይህን ሀሳብ ባልቃረነውም ነገር ግን አዘቅት ውስጥ ባለች ሀገር ውስጥስ የህዝቦች መደማመጥ በሌለበት ሀገር ውስጥስ በተከፈፈለ ማህበረሰብ ውሰጥስ  እላለሁ!! ለዚህም የህሊና ትዝብቴ መልስ የሚሰጡ የራሳቸውን ትንታኔ በመረጃ አስደግፈው  ህዝብን የወቀሰውን ህሊናዬን ተሳስቶል ብለው ውደ ግለሰብ አውረደው አንተስ!! በሚል ምፀት የሚያፈጥጡኝ አይጠፉም ይህን የሀሳብ ሙግት ይዤ ከበቴ ወጥቼ ለአመታት በተመላለስኩበት መንገድ ጉዜዬን ቀጠልኩ ጎዳናውን ይዤ በሁሳብ ሙግት ከህሊናዬ ጋር እየተሞገትኩ የጃቢርን ሱቅ አለፈኩት እዚ ሰፈር ከገባሁ ጀምሮ የማውቀው ባለሱቅ ነው የኔን እና የሱን ህይወት ስታዘበው ለውጥ አላይበት አልኩኝ ዝም ብዬ ሳስበው ምናልባት ባለሱቁ በርካታ በር በባንክ ይኖረው ይሆናል ግን የሱቁ ቀለም ያዉ ነው ለውጥ አላየሁበትም የሱቁ መጠን አልሰፋም አልጠበበም ያው ድሮ እንደማውቀው ነው።

የባለ ሱቁ አለባበስ ያው ድሮ እንደማውቀው ነው በሱቁ መስኮት ላይ ሆኖ ደንበኞቹን የሚጠብቅበት ሁኔታው  ያው ድሮ እንደማወቀው ነው። ሱቁ እቃ ልገዛ ስሄድ በመንግስት ላይ ስለግብር መጨመር የሚያነሳው ምሬት የው ድሮ እንደማውቀው ነው ምንም ለውጥ አላየሁበትም  አትርፎ እንኳን ቢሆን  በርካታ ሀብት ቢኖረውም ሀብቱ በህይወቱ ላይ ለውጥ ካላመጣ ያወ የዜሮ ድምር ነው። ያው እንደ ድሮው ያው... ያው.. ያው ነው ያው። ዝም ብዬ ሳስብ ብዙዎቻችን የቆመ አምሮ ታቅፈን ነው የምንዞረዉ የቆመውን አምሮችንን የሚነቃቃልን ሰው ያስፈልገናል ብቻ እራሴንም ሌላውንም እየወቀስኩ ታክሲ ውስጥ ገባሁ ታክሲ ውስጥ እንደ እድል ሆኖ ሰው ተጨናንቆ በሚቀመጥበት የመጨረሻ ወንበር ላይ እራሴን አገኝሁት ወደፊት ስመለከት በታክሲ ውሥጥ ያሉ በርካታ ጥቅሶች እና ተሳፈሪው ይታየኛል ከጥቅሶቹ መካከል‹‹ አትስራና ስትዞር ውለህ  እዞሩብኝ በል›› በዚህ ጥቅስ ውስጥ ብዙም መቆየት አልፈለኩም አይኔን ወደተሳፋሪዎች ማማተር ጀመረኩኝ

ሁሉም በራሱ ሀሳብ ውስጥ ይነዋልላል ታክሲው ልክ ሲነሳ እረዲዮኑም አብሮ ተነሳ አድማጮቻችን ሁለታ ሳአት ሁኖል ዜና እናሰማለን በቅድሚያም አርስተ ዜና ብሎ አገራ ከተሳፈረው መካከል አንዳንዱ እጁ ላይ ያለውን ሰአት  እየገረመመ አመሳከረ አንዳንዱም ሞባይሉን ከየኪሱ አውጥቶ ተገላመጠ ; ከመሽጋገሪያው ክላሲካል በውሀላ አርእስተ ዜናው መነበብ ተጀመረ።

በትላንትናው እለት በንትን ወረዳ ማንነቱ በልታቀ ቡድን አስር ሰዎች ተገደሉ የሰቆቃ ዜና.... ሁሉንም ተመለከትኳቸው ማንም ምንም አለመሰለው ለወትሮው ከንፈር የሚመጡ እናቶች እንኳን ዝምታን መርጠዋል ሁለተኛው ዜና ሲነበብ በትላንትናው እለተ ከንትን ወረዳ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ተፈኛቀሉ በርካቶችም ህየወታቸው አለፈ ማንመ የገረመው  አጣሁ ሁሉም በዝመታ ነው  ደንገጥ ያለ እንኳ የለም ሶስተኛው ዜና...  በትላንትናው እለት በንትን ከተማ በረካታ ሰዎች ለተቃዉሞ ወጥተው ከፀጥታ አካላት ጋር በተደረገ አለመግባበት በ10 ሰዎች ሞቱ በረካታ ህፃናት በደረሰባቸወ አደጋ ሆስቢታል መግበታቸው ታወቀ... አሁንመ     ሁሉም ዝም!!... እያለ የሰቆቃው ዜና ቀጠለ....ሌላ ሰቆቃ

... እና በታክሲ ውስጥ አብሬቸው ከተሳፈሩኩት በተለያየ እድሜ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ትዝብቴን ጀመርኩ እውነት ምንድነው የሰውን ነፍስ ከ ወፍ ነፍስ ያሳነሰው  ድሮ እንቅፋት ሲመታን እኔን ብሎ የሌላ ሰውን ሰቆቃ ለራሱ የሚመኝ በኔ ላይ ይሁን ሚለው ባህላችን የት ጠፋ ማን አጠፈው ማን ነጠቀን በእናቶቻችን እንደበት ውሥጥ ያለው የአዘኔታ ከንፈር መጣጣ የት ገባ ማነው ሞትን ተራ አደውርጎ ያለማመደን!! ማነው የክቡሩን ሰው ህይወት ተራ አድርጎ ያኮሰሰው ማነው ለሰው ለጅ ህይወት ማለፍ ደንታ የሌለን አድርጎ ያደነደነን ሞትን ተራ አድርጎ ያለማደንን በህሊናዬ ሳሰላስል አምሮዬ ላይ ሚዲያ መጣ በሀገራችን ያሉ ሚዲያዎች ሰቆቃ ከመዘገብ በቀር ለምን ? ማን?  አደረገው እነትና ሲሞቱ በምን ሞቱ?    ለምን ሞቱ ? እነሱ ሲሞቱ የሚመለከተው ምን እያረገ ነበር?  ብሎ የሚያፈጥጥ የሚወቅስ ሚዲያ እና ጋዜጠኛ የለንም... አዎ ዝም ብያ ሳስበው  ያለን ሚዲያ ሞትን የሚያለማምድ ሞትን ተራ ያደረጉ የሞት ዜናን የሚያንቆለጳጵሱ ሆነው በየቀኑ በሚያደርሱን የሞት ዜና ልባችን አደነደኑት የአዘኔታ  ባህላችንን አጠፉት ሞትን አለማመዱን!! የማይጠይቁ ፣የማይሞግቱ፣ ለምን ፣የማይሉ ሚዲያወቻችን ስንፍናቸው በግልፅ ታየኝ አንዱ ሚዲያ ላይ የተወራውን የሞት ዜና የሚደግሙ እንጂ በጉብዝና የሚመረምሩ ነገሩን የሚያጠሩ የህዝብ አንደበቶች አልሆኑለኝም።

ዝም ብያ ሳስበው  በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን  አፄ ሚኒለክ በሚለው መፃፍ ላይ ያለቸው አንዲት ሴት እና ምፀታዊ ግጥሞ ትዝ አለኝ ህዝብ በተሰበሰበት በየገበያወና በየ አደባባዩ ቴድሮስን እኩይ ስራ እያወገዘች የምትነቅፈው ያቺ ሴት ለኔ ጋዜጠኛ ናት ህዝቡን እንቅታለች ስልጣ በሌለበት    ንጉስን ማማት ነውር በሁነበት ሰአት የሰው ለጅ ሞት ከባድ እንደሆነ የሚያስነቅፍ፣ ለምን የሚሰብል እንደሆነ ተናግራለች። ንጉስ በማይከሰስበት ግዜ የባሎ ሞት ያንገበገባት  ለምን ብላ ጠይቃለች ተሞግታለች ማንንመ ሳትፈራ እንዲ ትል ነበር

‹‹ አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቶቼ ፣
አንድዶ እቃጥሎ ለብልቦ ፈጃቼ ፣
ሺ ፈረስ በውሀላው ሺ ፈረስ በፊቱ ፣
ሺ ብረት በውሀላው ሺብረት በፊቱ ፣
ይሄን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ ፣
ይህንን ሲሰማ ያጎራል ላመሉ ፤
ማናትም ቢላቼ ምንትዋብ ናት በሉ።

ይህን ግጥም ዝም ብዬ ሳስበው የሴትየዋ ድፍረት ገረመኝ ንጉሱ የሚቃወማቸውን ምላሱን በሚያስቆርጡበት ግዜ ለነፍሶ ሳትራራ ሰው ለምን ይሞታል? ብላ ትሞገት ነበር የሰው ነፍስ ክቡርነትን ትመሰክር ነበር ይን የሰሙት ህልመኛው ንጉስም ምንም አላሎትም ተግሳፆን ሰምተወ በዝምታ ይታዘቦት ነበር ፡፡ ከዛ ዘመን እስከ አሁን ዘመን ያለው የሚዲያ እድገት ሞትነ ማለማመድ የሞትን ዜና ተራ ማረግ ቢሆንብኝ ገረመኝ እናም ታዘብኳቹ!... ሚዲያወቻችን የህዝቡ አንደበት ሆናቹ ሞትን መዘገብ ብቻ ስራቹ የሆነ ለምን? የማትሉ የማትመረምሩ ሌላው ያለውን እንደገደል ማሚቱ የምታስተጋቡ የማታፋጥቱ .... ታዘብኮቹ!! እድሜ ለናንተ ዛሬ ሞት ተራ ነው ፡፡

ዛሬ የብዙ ሰዎች የሞት ዜና የስደት እና የመፈናቀል ዜና ማንም ግድ የማይሰጠው ተራ ወሬ ነው።
ስንፍናቹ ምትን አለማመድን፣ ታዘብኮቹ!! ስንፍናቹ የሰውን ነፍስ አረከሰብን የምንሰማው እንጂ የማናዳምጠው አደረጋቹህብን፣ የምታሽሞነሙኑት እና የምትቀባበሉት የሞት ዜና አፈዘዘን ለምን እንዳንል አንደበታችን ዘጋን የቆመ አዕምሮችንን አስታቀፈችሁን ታነቁናላቹ እንድ ታደርጉናላቹ ያልናቹ አንደበታችን ቃላችን የነበራችሁት እናንተ እዎ!!..... እናንተ... ሞትን አለማመዳቹህን እያልኩ በሀሳቤ ስሞገት መጨረሻው !!የሚለው የረዳቱ ድምፅ አባነነኝ።

DIGITAL MAGAZINE
CONTACT US
0912178520
0920019699

ESQUARE ADVERTISING PRESENTS

# IGNITE MIND FORUM

GRADUATION
DREAM



## DR MIHRET DEBEBE

SPECIAL GUEST

17 | 09 | 2011
11:00 AM
(LOCAL TIME)

AT:- METIKU HAILE HALL
(MEKELLE ARID CAMPUS )

ESQUARE
ADVERTISING

ቅንጫል
Digital Magazine

MU STUDENT UNION



የዛሬው የአውደብሩሀን ገፆች እንግዳችን ወ/ሮ ፍፁም ኪዳነማሪያም ትባላለች። ፍፁምን የዛሬው እንግዳችን ስናደርግ ከህይወት ተሞክሮዋ በብዙ መማር እንደሚቻል እርግጠኛ ስለሆንን ነው። ሀሳባችሁን እና አስተያየታችሁን እንጠብቃለን።

መልካም ንባብ!

-----------::----------

**ቅንድል**፦ በመጀመሪያ የዛሬው የቅንድል መፅሄት የአውደ ብሩሀን ገፆች እንግዳችን በመሆሽ በቅንድል መፅሄት ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

***ፍፁም***፦ እኔም የህይወት ተሞክሮዬ ወጣቱን ያስተምራል ብለሽ ይህንን እድል ስለሰጠሽኝ እጅግ በጣም አመሰግናለን።

**ቅንድል**፦ በቅድሚያ እስቲ ወደ ጥያቄዎቼ ከመግባቴ በፊት ፍፁም ኪዳነማርያምን ለአንባቢያን አስተዋውቂልን?

***ፍፁም***፦ እሺ እራሴን ለማስተዋወቅ ከስሜ ነበር የምጀምረው። እስተዋውቀሽኛል፤ ባለትዳርና የአንድ የዘጠኝ ዓመት ልጅ እናት ነኝ።
ትምህርት የህይወቴ መሰላል ነው። በፕሮጀክት ማኔጅመንት የማስተርስ ድግሪና የአለም አቀፍ ድህረ ምረቃ ዲፕሎማ አለኝ፤ በማኔጅመንት ድግሪ ሲኖረኝ በላይብራሪ ሳይንስ ደግሞ ዲፕሎማ አለኝ፤ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አጫጭር ስልጠናዎችን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭም በመውሰድ ሰርተፍኬቶችን አግኝቻለሁ። ወደፊት ዶክትሬቴንም ለመስራት አቅጃለሁ።
በሥራ ደግሞ ከላይብራሪያን እንስቼ አሁን እስከደረስኩበት የሲኒየር ማኔጅመንት እርከን ላይ ለመድረስ የተለያዩ ድርጅቶች ማለትም በዩኒቨርስቲ፣ በሌላ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆነ፣ በገር በቀልና በአለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተባበሩት ድርጅትን ጨምሮ ፣ በመጨረሻም በቢዝነስ ድርጅት ውስጥ በጠቅላላው ከ20 ዓመት በላይ ሰርቻለሁ።
በነገራችን ላይ የራሴም ድርጅት አቋቁሜ ለጥቂት ጊዜ በግል ስራ ተሰማርቼ ውጤታማ መሆን ስላልቻልኩ ዘግቼዋለሁ። በአጠቃላይ ያመንኩበትንና የፈለግኩትን ነገር ለማድረግ የምሞክር ከውድቀቴ እየተማርኩ ወደፊት የምጓዝ ሰው ነኝ።

**ቅንድል**፦ እሺ አመሰግናለሁ ፍፁሜ በተለያዩ ዘርፎች ላይ በተለይ በአስተዳደርና በአመራር ዙሪያ ስትሰሪ ቆይተሻል ታድያ መሪ መሆን ላንቺ እንዴት ይገለፃል?

***ፍፁም***፦ መሪነት ጥበብ (አርት) ነው።
ጥበብ ደግሞ ለኔ እንደ ጥልቅ ባህር ነው። ጥልቅ ባህር ከውጭ የምናየው ደስ የሚለውን የተንጣለለ ውሀ ነው። ውስጡ ስትገቢ ግን ብዙ ነገር አለው፤ ለህይወትሽ ምግብ የሚሆኑ አሣዎችን ታገኛለሽ፣ የሚውጥሽ አሣ ነባሪ ሊያገኝሽ ይችላል፣ አልያም አንቺም የማትገለገይበት አንቺንም የማያጠቃሽ የባህር ውስጥ ፍሪ ታገኛለሽ፣ በጥልቀቱ ልክ ደግሞ ቋጥኝ ድንጋይም ሊገጥምሽ ይችላል።

እንግዲህ ከዚህ ባህር የምትፈልጊውን ጥቅም ከውስጡ ለማግኘት ብዙ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብሻል፤ የባህሩን ባህርይ ጠንቅቆ ማወቅ፣ **ዋናተኛ መ**ሆን፣ ጥሩ መርከበኛ መሆን፣ ጀልባ ቀዛፊ መሆን...ወዘተ። ይህንን ሳታደርጊ በድፍረት ከገባሽ ሰምጠሽ ትቀርያለሽ አልያም በአሣ ነባሪ ትበያለሽ። መሪነትም ቅድመ ዝግጅት ይፈልጋል፤ ለማወቅ መትጋትን፣ የአዋቂዎችን አገዛና ተሞክሮ በመጠየቅ ልምድ ማግኘትን፣ ሌሎች ተከታዮችን ማብቃትን፣ የተሰጠሽንም ኃላፊነት በብቃትና በታማኝነት መወጣት መቻል ማለት ነው። እንዲሁም መሪ መሆን ማለት ዛሬም ሆነ ከፊት ለፊትሽ ሊገጥሙሽ የሚችሉትን ተግዳሮቶች ለማለፍ ሁሌም ክፍት አእምሮ እንዲኖርሽ ያስፈልጋል።

**ቅንድል**:- ፍፁም ወጣትነትሽን እስቲ አስታውሺን ምን ማድረግ ያስደስትሽ ነበር?

**ፍፁም**- በወጣትነቴ ሁለገብ የምባል ዓይነት ሰው ነበርኩ፤ ከምንም በላይ ለትምህርቴ ትኩረት እሰጣለሁ። መማር በጣም ያስደስተኛል። ከት/ቤት የሚያስቀር ህመም እንኳን ሲገጥመኝ ከመታመሜ ይልቅ ከት/ቤት መቅረቴ ነበር የሚያስለቅሰኝ። ከትምህርቴ ውጭ በትምህርት ቤቶቼ በሚደረጉ የተለያዩ ክበባት ተሳታፊ ነበርኩ፤ ሯጭ ነበርኩ አክሮባተኛ ነበርኩ ገጣሚና ተራኪም ነበርኩ። የት/ቤት ሚኒ ሚዲያ መሪም ነበርኩ። በምማርበት ት/ቤት ክፍል ውስጥ አስተማሪ ከቀረ በራሴ ተነሳሽነት ጥያቄ እያዘጋጀሁ በመጠየቅ ተማሪዎችን ማገዝ ያስደስተኝ ነበር። ከት/ቤት ውጭ በሰንበት ት/ቤት ተማሪና ዘማሪ ነበርኩ፤ ሠፈር ውስጥም በጣም ተጫውቼ ነው ያደግኩት፤ እግር ኳስ ሳይቀር ተጫወቻለሁ። ከዚህ ውጪ ደግሞ በጣም የሚያስደስተኝ አረጋውያንንና አቅመ ደካሞችን እንዲሁም በድህነት የሚኖሩትን መርዳት ነበር።

ይሄ ደግሞ በተለይ የእናቴ መልካም ሴትነት፣ የሰንበት ተምህርት ቤትና ያደግኩበት ሰፈር ያስተማረኝ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ውጤት ነው ብዬ **አምናለሁ**።

**ቅንድል**:- የህይወት መርሆዬ ይሄ ነው የምትዪው ነገር ካለ ብታካፍይን?

**ፍፁም**- እኔ የህይወት መርሆዬ ለራሴና ለቤተሰቤ የተሻለ ህይወት እንዲኖረን ተግቶ መስራት፣ እውቀት ጥልቅ ስለሆነ ያለማቋረጥ መማር፣ የኔን እድል ያላገኙትን እንዲያገኙ መምከርና መርዳት። ይህንን ለማድረግ የማይችሉትን አቅመ ደካሞችና በድህነት የሚኖሩትን አቅሜ በፈቀደው ሁሉ መደገፍ ነው።

**ቅንድል**:- ለትምህርት ያለሽ አቋም ጠንካራ እንደሆነ እውቃለሁ በዚህ ዙሪያ ምን ትያለሽ?

**ፍፁም**- "ሠውን ሰው የሚያደርገው ትምህርት ነው!" ይህ የኔ አቋም ነው። ፈጣሪ ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥረው ሙሉ አድርጎ ነው። ለዚህም ሙሉነት ማረጋገጫ አእምሮን እንደመሳርያ እንጠቀምበት ዘንድ ፈጥሮልናል። ከዛ በኋላ ግን የተሰጠንን አእምሮ እውቀትና መልካም ነገርን እየሰጠን ካላደግነው እንደኛ ማን ሀብታም አለ! ሀብት ስል ገንዘብ ብቻ አይደለም። ውስጣዊ እርካታ፣ በራስ መተማመን፣ በፈተናዎች ያለመንገዳገድ፣ ብልህነት፣ ከራስ አልፎ ለሌሎች መትረፍ...ወዘተ የእውቀት ውጤቶች ናቸው፤ በመማርና በማንበብ የታገዘ እውቀት። ይህንን ስል በመማር ሀብት አይገኝም እያልኩ አይደለም። አሁን የምኖረው የተሻለ ህይወት የመማሬ ውጤት ነው። ትምህርት ብቸኛ መሣርያ ባይሆንም የድህነት ማሸነፍያ መሳርያም ነው። እኔ ለትምህርትና ለተለያዩ ስልጠናዎች የማወጣው ወጪ በጣም ብዙ ነው ግን ምንም ቆጭቶኝ አያውቅም።

የሚቆጨኝ መማር እየፈለግኩ አቅም ሲፈትነኝ ብቻ ነው። ወደፊትም እማራለሁ፤ እስትንፋሴ እስክታቆም ወይንም አቅሜ እስኪደክም አላቆምም።

**ቅንድል**:- በህይወቴ ፈተና ሆኖብኝ አልፌዋለሁ የምትይው ነገር አጫውቺን

**ፍፁም**:- በጣም ብዙ ፈተና ደርሶብኝ ያውቃል። ለወጣቶች ጠቃሚ ናቸው የምላቸውንና ወጣት ሆኜ የገጠመኝንና እንዴት እንደተወጣሁት ላጋራችሁ፤ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የተማርኩት አዲስ ከተማ ከፍተኛ ት/ቤት ነው። ይህ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ የአውቶቡስ ተራ ወረድ ሲልም መርካቶ ነው ያለው;; አርብ አርብ መምህራንና የሰራተኞች ስብሰባ ስለነበር እያንዳንዱ የትምህርት ክፍለጊዜ በግማሽ ይቀነስና በጊዜ እንለቀቅ ነበር ታድያ በአብዛኛው ተማሪዎች በቀጥታ ወደቤታቸው መግባት አይፈልጉም ነበር። ፊልም ቤት ይገባሉ፤ በቡድን በመዟዟር ለቀቅ ያለ የቤተሰብ ቁጥጥር ባሉባቸው ጓደኞቻውቸ ቤት በመሄድ በሙዚቃና በመዝናኛ ስም ሌሎች ከሱስ ጋር የተገናኙ ተግባራት መፈፀም የተለመደም ነበር። ይህንን የማያደርጉ ተማሪዎች በዘመኑ አጠራር "ፋራ" ማለትም ኋላ ቀር በመባል ይሳቅባቸዋል ከዛም ባለፈ ይገለሉ ነበር;; ታድያ ብዙዎች ይህንን ፍራቻ ይቀላቀላሉ፤ ከማይወጡት ሱስ ይዘፈቃሉ፤ ከትምህርታቸውም ይስተጓጎላሉ። እኔ በተለይ ደግሞ በነበረኝ ሥምና ዝና ማለትም በትምህርትም ሆነ በተለያዩ ክለባት ተሳትፎ ብዙዎች (ለማሰናከል ከማሰብ ላይሆን ይችላል) አብሬያቸው እንድሆን ስለሚፈልጉ በየሳምንቱ ይጎተጉቱኝ ነበር። እኔ ግን አራት ዓመት በዛ ት/ቤት ስማር አንድም ቀን ፊልም አይቼ የማላውቅ ፋራ ነበርኩ፤ ምንም ዓይነት በጓደኞች ግፊት የሚደረግ መዝናኛ ተሳትፌ አላውቅም ነበር። ይህ ባህርዬ ቀጥሎ በዩኒቨርስቲ ህይወቴም ከጫትም ሆነ ከማንኛውም ሱስ ከተገለሉ ተማሪዎች መሀል ነበርኩ። ሌሊት ሲያጠኑ አምሽቶ ቀን መማር ምን ያህል የእንቅልፍ ዳተኛ እንደሚያደርግ እናውቃለን። እንቅልፋምነቴ ግን ከዛሬ የህይወት ህልሜ አላሰናከለኝም። በጊዜው ከእኩዮች የተለየ ሆኖ መታየት የሚያሳፍርና ጓደኛ የሚያሳጣ ሊመስለን ይችላል፤ የተገለልንም ልንሆን እንችላለን። የማታ ማታ ግን ድሉ ከምንም በላይ እርካታ ይሰጣል። ምክንያቱም ያኔ የተጀመረ ሱስ ብዙዎችን ከመንገዳቸው አሰናክሏል፤ ተሳክቶላቸው በንግድም ይሁን በተለያዩ ሥራዎች የተሰማሩትም ቢሆኑ ዛሬ በጉልምስናቸውም የብዙዎችን ህይወት እያመሳቀለ እንደሆነ አውቃለሁና

**ቅንድል** : በተለያዩ ክበባት፣ ዝግጅቶች እና የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ ትሳተፊያለሽ? ጥቅሙ እስከምን ድረስ ነው?

**ፍፁም**:- ክበባት፣ ዝግጅቶችና በጎ አድራጎት ስራዎች የየራሳቸው ጥቅም አላቸው። ከክበባት ስጀምር በኤውብ፣ ቶስትማስተርስና ሶሳይቲ ኦፍ ኢውማን ሪሶርስስ የረዥም ጊዜ አባልና በተለያዩ የቦርድ አመራሮችም ላይ አገልግያለሁ፤ ይህ የኔን እውቀት ከማሳደጉም ባሻገር ከማገኛቸው ሰዎችም ብዙ የህይወትና የሙያ ልውውጥ አደርጋለሁ። በተጨማሪም የኔ ተሳትፎ ለሌሎች ወጣቶችና እንደኔ ላሉ ጎልማሶች አገልግሎት መስጠት ይሆናል ማለት ነው;; ሰው እውቀት የሚያገኘው ከትምህርትና ስልጠና ውጪ በእንደዚህ ያሉ ክበባት ሙሉ ተሳትፎ በማድረግም ጭምር ነውና!
ዝግጅቶች በተለይ የኪነጥበባት ፕሮግራሞችና ወቅታዊ የሆኑ የሁሳብ ልውውጥ መድረኮች ያዝናኑኛል፣ ጓደኞች አፈራባቸዋለሁ እንዲሁም የኔንም ሀሳቦች ለሌሎች አጋራበታለሁ።
በጎ አድራጎት አገልግሎት መስጠት ደግሞ ህይወቴ ነው! በመስጠትና በጎ በማድረግ የማገኘው ደስታ ከደስታዎች ሁሉ በላይ ነው። ደግ ሆኜ አይደለም ነገር ግን የበለጠ ተጠቃሚ በመሆኔ ነው። እኔ እድሉን በማግኘቴና በመጣሬ ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። ከሁሉም በላይ ጤና ሰጥቶኝ ጤናማ ነገር እንዳደርግ ፈጣሪ እድሉን ሰጥቶኛል። ይህንን እድል ደግሞ ላላገኙት መስጠት ያስደስተኛል፤ የዜግነት ግዴታዬም ነው።

**ቅንድል** : አንድ ነገር የመቀየር እድል ቢሰጥሽ በኢትዮጲያ ውስጥ የምትቀይሪው ነገር ምን ይሆናል?

**ፍፁም**:- አንድ ነገር ብቻ ከሆነ የምቀይረው ሰዎች የሥራን ክቡርነት ተረድተው በሥራ ላይ ያሉት በሙሉ ልብና በየኔነት ስሜት እንዲሰሩ ማድረግ፣ ትናንሽ ሥራዎችንም አክብረው እንዲሰሩ ማድረግና እየሰሩ ያሉትንም እንዲያ**ከብሩ** ማድረግ ነው።
ምሣሌ ለመጥቀስ የጎዳና ላይ ፅዳት ሠራተኞችን ይመለከቷል፤ ፊታቸውን የሚሸፍኑት እኮ ከቆሻሻ እራስን ለመከላከል በሚል ሽፋን ከማህበረሰቡ ለመደበቅ ነው። ይህ ኋላቀርነታችንን ማጥፋት ብንችልና በስራ ክቡርነት የሚያምን ማህበረሰብ መፍጠር ብችል ዋነኛ ጠላታችን የሆነውን ድህነታችንን ድል እንደምናደርግ አምናለሁ።

**ቅንድል**:- ሴት ነሽ እናት ነሽ ሚስት ነሽ እነዚህን ነገሮች ከሙያዊ አለም ጋር(professional world) ጋር እንዴት ማመጣጠን ይቻላል?

**ፍፁም**:- ለኔ የዚህ ሁሉ ሙያ ባለቤት መሆኔ በቅድምያ ያኮራኛል። በነገራችን ላይ እኛ ፕሮፌሽናል ሴቶች ድርብርብ ጫና ነው ያለብን። አንዳንዴ ከትልቅ የማኔጅመንት ስብሰባና ፕሮቶኮል ወጥተሽ እራስሽን ሌላ ትልቅ ግርግር ያለበት መርካቶ ወይም ገበያ አስቤዛ ስትገዢ ታገኚዋለሽ። ከዛ መልስ ደግሞ ማህበራዊ ህይወት ግድ ነውና የታመመ መጠየቅ የሞተ መቅበር የመሳሰሉትን ታከናውኛለሽ፤ እቤት ስትገቢ ልጅሽ/ልጆችሽ የቤት ስራ መስራታቸውን ታረጋግጫለሽ ያልገባቸውን ለማስጠናት አስተማሪ ትሆኛለሽ፤ ከዛ ወደ ማእድ ቤት ገብተሽ ከረዳትሽ ጋር ጉድጉድ ትያለሽ...ወዘተ። በጣም ይደክምሻል አንዳንዴም ሊሰለችሽ ይችላል ሰው ነሽና፡ ይሁንና ከምንም በላይ ለሰዓት አጠቃቀምሽ ዋጋ ስለምትሰጪ ትችይዋለሽ። ሌላው ደግሞ እኔ ሁሌም መልካም ነገርን በማሰብ እራሴን በጣም እቃቃለሁ። እኔ ይህ ሁሉ ጫና ቢኖርብኝም ብዙ ያሸነፍኩት ነገር አለ፤ በትምህርትና በኢኮኖሚ እራስን መቻል። ይህ ባልተሟላበት ባል ካላቸው ከእነርሱ በሚያገኟት ትንሽ ገንዘብ ያም በሌለበት ጥቃቅን ንግዶች ላይ በመሰማራት በሚያገኙት ትንሽ ገቢ ልጆቻቸውን በችግር የሚያሳድጉ ሴቶችም እናቶችም ሚስቶችም የሆኑ እህቶቼን አስባለሁ። አልፌም እነሱን የምደግፍበትን ማሰብ እጀምራለሁ። ያኔም የኔ ሸክም በጣም ይቀለኛል። ህይወት ሁሌም አንፃራዊ ናትና!

**ቅንድል**:- ፍፁምን ምን ያዝናናታል?

**ፍፁም**:- ብዙ ነገር፤ ጉዞ እወዳለሁ፤ የሀገራችን ታሪካዊ ቦታዎች በአብዛኛው ጎብኝቻለሁ፤ ሰዎችን መተዋወቅና መልካሞችን ጓደኛ ማድረግ፣ የተቸገሩን መርዳት በጣም ያስደስተኛል በተለይ የሚፈልጉትን ነገር አቅም ፈቅዶልኝ ሳደርግላቸውና ሲደሰቱ ሳያቸው ምን ልበልሽ! መፅሐፍትን አነባለሁ፤ ሙዚቃ በጣም ያዝናናኛል፤ አልፎ አልፎ ሲኒማም አያለሁ፤ የአማሪኛም የእንግሊዝኛም።

**ቅንድል**:- አርአያዬ ነው የምትዪው ሰው ማነው?

**ፍፁም**:- እኔ የብዙ ሰው ውጤት ነኝ። በዋናነት አርአያዬ ግን እናቴ ናት። በተለይ ወጣት ሆና እኛን ያለአባት ስታሳድግ የሚገጥማትን ፈተና ተቋቁማ የትምህርትን ጥቅም አስረግጣ በማሳመን ውልፍት እንዳልል አድርጋ ያሳደገችኝና ፡ማንኛውም ብልጭልጭ ነገር የትም እንደማያመልጠኝ ያስረገጠችልኝ፡ ታማኝ መሆን በህይወት ዘመኔ ሞገስ እንደሚሆነኝ ያስተማረችኝ ፡ለሰዎች መልካም ሆና መልካምነትን ያስተማረችኝ ፡በጣም ቆፍጣና እመቤት ናት። አሁንም እንኳ አቅሟን ህመም ቢፈትነውም ብሩህ አእምሮ ነው ያላት። አማካሪዬና ጥሩ ጓደኛዬ ናት። ሌሎች በህይወት ገጠመኜ ማለትም በትምህርቴ፣ በስራዬ እና በተለያዩ ማህበራት ተሳትፎዬ ያገኟቸው መልካም ሰዎችና እንዲሁም ጓደኞቼ ብዙ ናቸው።

ሥም ልዘርዝር ብል አንድ ገፅ አይበቃኝም። የአንድ ቀን እንኳን ምክር እንኳን ሰጥተው ህይወትሽን የሚቀይሯት ሰዎች በሰጡሽ ምክር ልክ እድሜ ልክሽን ትከተያቸዋለሽ። እድሜሽን ሙሉ ታመሰግኛቸዋለሽም።

**ቅንድል**:- እንግዲህ የመፅሀፍ ጥቆማ ላይ ደርሰናል ማንበብ ትወጃለሽ? ሰው ሁሉ፡ምን የሚለውን መፅሀፍ ቢያነብ ደስ ይልሻል?

***ፍፁም***:- ማንበብማ መውደድ ብቻ ሳይሆን የአእምሮዬ ዋነኛ ምግብ ነው። ሁሉም ሰው በየዘመኑ ፍቅር ህይወት ይኖረዋል። የሀገር፣ የቤተሰብ፣ የተቃራኒ ፆታ፣ የጓደኛ...ወዘተ ለዚህ ከአማሪኛ የሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር ለኔ ሙሉ ነው።
የሲሳይ ንጉሱ ሰመመን ደግሞ በተለይ ዩኒቨርስቲ ልገባ ስል በማንበቤ የሚጠብቀኝን ተግዳሮትና መልካም ነገርም እንዳውቅ ስለረዳኝ ባለውለታዬ ነው።
የከበደ ሚካኤል ተረትና ምሳሌም የቁምነገር ጥሩ አስተማሪ ነው።
የእንግሊዘኛ ቋንቋ ደግሞ "The 7 Habits of Highly Effective Families, by Stephen & Covey, The magic of Thinking Big by David J. Schwartz, በተለይ ደግሞ መሪ ለሚፈልጉ ሴት ወጣቶች "Nice Girls Don't Get the Corner Office by Loise P. Frankel"

**ቅንድል**:- ከልጅ እስካዋቂ ሊያየው የሚገባ ድንቅ ፊልም የምትይው ካለ?

***ፍፁም***:- የወላጅን ጥልቅ ፍቅር ያየሁበትን ታዋቂው Denzel Washington የተወነበት "John Q" የፍቅርን እና የእምነትን ሀያልነት ያየሁበትንና ዝነኛዋ Julia Roberts የተወነችበት "Eat Pray Love"

**ቅንድል**:- ለወጣቶች ማስተላለፍ የምትፈልጊውን መልዕክት ምንድነው?

***ፍፁም***:- ህይወት ረጅም መንገድ ናት፤ ብዙ በተጓዝን ልክ ብዙ ድሎችም ፈተናዎችም ይገጥሙናል። በፈተናዎች ተሰናክሎ ላለመውደቅ እራስን ማጀገንና ድል አድራጊ መሆን ያስፈልጋል። በጊዜያዊ ደስታ እራስን ከመደለል ይልቅ ለዘላቂ ደስታ ተግቶ መማርና ስራን ሳይንቁ ተግቶ መስራት ሙሉ ያደርጋል። ፍሬውም ሁሌም ያማረ ይሆናልና። ራስን ስኬት ፍለጋ አቋራጭ መንገድ መጠቀምና ሌሎችንም ሰዎች መጉዳት ዋጋ ያስከፍላል። ለቁጭት እድል አትስጡት፤ ይህ ደግሞ ቁርጠኝነትን ይጠይቃልና ቁርጠኛ ሁኑ! እምነት ይኑራችሁ እላለሁ። በክርስትናም ይሁን በእስልምና ሀይማኖት ያለን ሰዎች አንድ አናጢ ነው ያለን ይህም ፈጣሪ አምላካችን ነው። ነገሮች እንኳን ከአቅም በላይ ሲሆኑብን እንኳ ለበጎ ነው ብለን እንፅናናለን፤ ለተሻለ ነገም ተስፋ በማድረግ እንተጋለን።

**ቅንድል**: እኔ ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ አንቺ ቀረ የምትዪው ነገር ካለ እድሉን ልስጥሽ።

***ፍፁም***:- ለወጣቶች የምመክረው ሶሻል ሚዲያውን እንደዚህ ጠቃሚ ምክር ከሚሰጡ ሰዎች ጋር መገናኛ ቢያደርጉት ለህይወት አሰናካይ ከሆኑ መልእክቶች እራሳቸውን ቢያቅቡና መልካሙን መንገድ ቢከተሉ መልካም ነው እላለሁ።

**ቅንድል**:- የአውደ ብሩሀን ገፅ እንግዳችን ስለሆንሽ እና ከአውደ ብሩሀን ገፆችሽ ስላካፈልሽን ከልብ እናመሰግናለን።

***ፍፁም***:- እኔም እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።



በ ሳኦል አክሊሉ
aklilu7kemal@gmail.com

# ጥቁር ምስል
## ክፍል-2

ጥቁር ምስል
ክፍል 2
ሶኒ ሮጦ መታጠቢያ ቤቱ ሲደርስ በሩ ከውስጥ ተቆልፏል፡፡ በሩን በሀይል እየደበደበ ‘ቃለአብ?! አንተ ቃለአብ?! ቃልሽ በሩን ክፈት!!’ የቃለአብ ድምፅ ሊሰማ አልቻለም፡፡ መታጠቢያ ቤቱን ለመስበር ወደኋላ ተንድርድሮ ሮጦ በእግሩ በሩን መታው፡፡ በሩ ንቅንቅ አላለም፡፡ ‘ቃልሽ በሩን ክፈት!!’ በሩን አንዴ በእግሩ ፣ አንዴ በትከሻው ለመስበር እየታገለ ሲያቅተው ወደ ተማፅኖ እየተመለሰ ‘ቃልሽ በሮዛ ይዝሃለሁ እባክህ በሩን ክፈት!!’
የቃለአብ ጆሮ ላይ የሶኒ ድምፅ ያቃጭላል፡፡ ቃለአብ ከጭንቅላቱ የሚፈሰው ደም የእውነት ደም አልምስል አለው፡፡ ደሙ እየሰፋ እየሰፋ መታጠቢያ ቤቱን ሊያዳርስ ትንሽ ቀርቶታል፡፡ የሶኒ ጩኸት በሰመመን ውስጥ ሆኖ ይሰማዋል፡፡ ‘ቃልሽ በሮዛ ይዝሃለሁ በሩን ክፈት!!’
‘ሮ......ዛ’ አለ ቃለአብ በስቃይ ውስጥ ሆኖ ስሟን ለመጥራት አቅም እያነሰው፡፡ ስሟን ሲጠራ የመጀመሪያ ትውውቃቸው በሃሳቡ መጣ፡፡

ካምፓስ ውስጥ ነው፡፡ ሮዛ ሃንዳውቶቿን ወደ ደረቷ አስጠግታ አቅፋ እየተራመደች እያለ ቃለአብ ከኋላዋ ስሟን እየጠራ ይመጣል ‘ሮዛ ሮዛ’ ሮዛ ትቆማለች፡፡ አጠገቧ ደርሶ ይቆማል፤ ሮዛ ግራ ተጋብታ ቃለአብን ስትለመከተው ‘id መንገድ ላይ ጥለሽ ነው’ ብሎ ይሰጣታል፡፡ ‘ታዲያ ስሜን ከየት አወቅከው?’ ቃለአብ እንደመሳቅ ብሎ ‘ከ idሽ ነዋ’ አላት፡፡ ኦው ብላ ተገርማ ትስቃለች፡፡ ፈገግታዋን ሲያይ ደንግጦ ቀረ፤ የፈተና የአሳይመንት ጭንቀት ድራሻቸው ጠፍቶ ሮዛ አሳይመንት ሆነች፤ የችግሮቹ ሁሉ ማብቂያ የእሷ ፈገግታ ይመስል ፈገግታዋ ውስጥ ተሰምቶት የማያውቀው አይነት ምቾት ተሰማው፡፡

‘እሺ አመሰግናለሁ’ ብላ ልትሄድ ስትል እንድትቆይ እይፈለገ ‘አመሰግናለሁ ብቻ?’ አላት፤ አሁንም የመጀመሪያውን ብርሃን የሆነ ፈገግታዋን እየደገመችው ‘ሌላ ምን ልበል ታዲያ?’ አለችሁ፡፡ ቃለ አብ ግራ ገባው፤ ብዙ አስቦ የመጣለትን ቃል ተነፈሰ ‘የእኔን id ወድቆ ካገኘሽው ትመልሽልኛለሽ?’ አላት ፤ ቀሽም ጥያቄ መሆኑ የገባው ቆይቶ ነው፡፡ ሮዛ የማያቆም ሳቅ እየሳቀች ፤ የእሷን ፈገግታ ተከትሎ እሱም የሞኝ ፈገግታ እያሳያት ሲስቅ ፤ ሳቋን እንዳቆመች ‘እንዴ ምን ጥያቄ አለው?’ ብላ እየሳቀች ጥላው ትሄዳለች፡፡ ቃለአብ ሁለት እርምጃ ቀድሟት ሲያልፍ ሮዛ ግራ ተጋብታ ‘ወደ ኋላ እየሄድክ ነበርኮ’ አለችው፡፡ ‘አንዳንዴ እግር ወደፊት እየሄደ አእምሮ ደግሞ ወደ ኋላ ሊራመድ ይችላል’ አላት ምን ለማለት እንደፈለገ ለራሱም በትክክል ሳይገባው እና በመልሱ ብርሃን ፈገግታዋን እየተመኘ ፤ ‘አእምሮህ የሚፈልገው ሌላ እግርህ የሚያደርገው ሌላ ስለሆነ ነዋ’ አለችው ፈገግታዋ ሳይጠፋ፡፡ ‘ለማንኛውም አእምሮህን እና እግርህን አስታርቃቸው እ?’ አለችው በፈገግታዋ ቀኑን አብርታለት እየሄደች፡፡

ከሳምንት በኋላ

ሮዛ ለቃለአብ idውን እየመለሰችለት ‘ኸረ ቃልአብ በፈጠረህ idህን ተጠንቅቅህ ያዝ ፤ ሰው በሳምንት ስድስት ጊዜ idውን ይጥላል?’ አለች በግርምት እየሳቀች፡፡ እሱ id ሲጥል እሷ ስትመልስልት ቀናት ነጎዱ ፤ ቃለአብ idውን መጣል ያቆመው ሮዛ ፍቅረኛው ከሆነችበት እለት ጀምሮ ነው፡፡

ቃለአብ የምስኪን ጓደኛው ጨኸት መሃል ላይ ገብቶ ከደስታው አለም መለሰው ፤ 'ቃለአብ?! አንተ ቃለአብ?!' ይለዋል ሶኒ የቃለአብን ትከሻ ይዞ እየነቀነቀ። ሶኒ በሩን ሰብሮ ከገባ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የቃለአብን ስም እየተጣራ ነው። ቃለአብ ሶኒን ለማየት ሞከረ ግን አልቻለም። አይኖቹ ድክምክም ብለው ጉልበት ሲያጡ ታወቀው። አንገቱን ለማንቀሳቀስ ሞከረ እምቢ አለው። ወገቡ ላይ ያለውን ህምም ለማስታገስ እግሩን ወደራሱ ሊሰበስብ ሞከረ፤ አልቻለም፤ በእጁ የወገቡን ህመም ነካክቶ ለማስታገስ አስቦ እጁን ሊያንቀሳቅስ ሲል እጁም አልታዘዝ አለው። ትንፋሹ ሲደክም ታወቀው። 'ይህ የመጨረሻ ቀኔ ይሆን?' አለ በውስጡ የደበዘዘውን የጓደኛውን ምስል በደንብ ለማየት እየተመኘ እና ወደዚህ ሱስ የገባበትን ቀን እየረገመ።

ከሩቅ የሚሰማው የአንቡላንስ ድምፅ እየቀረበ ፤ እየቀረበ ሲመጣ ይሰማል ... ቃለአብ አንቡላንሱ ውስጥ ሮዛ እንድትኖር ተመኘ ፤ 'ዛሬ የመጨረሻ ቀኔም ከሆነ ይቅርታ ጠይቂያት ነብሴን ላሳርፋት ፤ ከመሞቴ በፊት ማየት የምፈልገው የመጨረሻ ምስል የሮዛን ነው ፤ ሞቸም ቢሆን ምስሏን ከኔ ጋር ይዤ መሄድ እፈልጋለሁ' አለ በውስጡ፤ አቅም አግኝቶ ይህንን ቃል ለሶኒ ቢነግረው ተመኘ።
ቃለአብ ድንገተኛ ክፍል ከገባ 40 ደቂቃ አለፈው ፤ ሶኒ ደንግጧል ፤ ለሮዛ ጀርባውን ሰጥቷት ቆሟል ፤ ሮዛ እየተንሰቀሰቀች ፈጣሪን በድምፅ አልባ ቃል እየለመነች ታለቅሳለች ፤ የድንገተኛ ክፍሉ በር ተከፍቶ ዶክተሩ ወጣ...
ይቀጥላል ...
ሳኦል አክሊሉ
ሚያዚያ 28/2011 ዓ.ም



ቅንድል
NEW VERSION OF KENDIL

# STOP HATE SPEECH!

ቅንድል ዲጂታል መፅሔት ከቲክቫህ ኢትዮጵያ እና ከሌሎች ተባባሪ አዘጋጆች ጋር በመሆን በመቀሌ ዩኒቨርስቲ "የጥላቻ ንግግር ይቁም!" በሚል መሪህ ቃል ለተከታታይ ሁለት ቀናት(ሚያዝያ 26/27) ታላቅ የኪነጥበብ መድረክ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዚህም ምሽት ፕሮፌሰር ክንደያ ገ/ሂወትን ጨምሮ ብዙ ታላላቅ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተካፍለው ነበር፡፡

የዚሁ ዝግጅት አካል የነበረው የደም ልገሳ፡የፅዳት፡ የህፃናት መሳደግያ ማዕከሎችን የመጎብኘት ስራም ከቲክቫህ ቤተሰቦች እና ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ በተወጣጡ ተማሪዎች ተከናውኗል፡፡



እንደሚታወቀው የጥላቻ ንግግርን ለማውገዝ በየዩኒቨርስቲው የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሀሳብ የመለዋወጫ መድረክ በቲክቫህ ኢትዮጵያ አዘጋጅነት እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የየዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በንቃት እየተሳተፉበት ይገኛሉ፡፡ ይህ መሰሉ መድረክ ለሀገር ያለው ፋይዳ ወሳኝ ከመሆኑ አኳያ እና የዚህ ችግር ተዋንያኑም ሆነ የዚህ ገፈት ቀማሹ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንደመሆኑ ይህን መሰሉ ዝግጅት በዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ተገድቦ ሊቀር አይገባም፡፡

በመሆኑም የመንግስት እና የግል መስሪያ ቤቶች፡ የሀይስኩል እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች፡ ክበባት ይህን መሰል ዝግጅቶች በማዘጋጀት ወጣቶች የምንመካከርበት፡ ሀሳብ የምንለዋወጥበት እና ለሀገራችን እምዬ ኢትዮጵያ አንዳች በጎ ነገር የምናበረክትበት መድረኮች እንዲፈጠሩ አደራ እንላለን፡፡

#ቅን #ምክንያታዊ #ሀገር ወዳድ ዜጋ እንሁን!!



በያብስራ ካሳ



# የ30 አመቱ ሽማግሌ

መቼም ስለፊት ሲነሳ ስለቁንጅና መወሳቱ አይቀርም ። ብንወድም ብንጠላም ቁንጅና ማለት ደሞ መርገፍያ ጊዜውን እንደሚጠብቅ የጠዋት ጤዛ ነው ። እዚህ ጋር ታድያ ሁሉ በቀጠሮ እንደሚመጣ እና እንደሚሄድ ልብ እያልን። እስኪ እንደው ግን ድንገት እንድቀን ክእንቅልፋችን ስንነቃ አለን ያልነው የወጣትነት ደምግባታችንን ተሰውሮ ብናገኘውስ ? በቃ እምጥ ይግባ ስምጥ አይታወቅም ፤ ብቻ በማለዳ መስታወታችንን ስናይ በድሜያችን ጠዋት ላይ ገርጅፈን ውበታችን ጠውልጎ ፤ ያን የምንሸሸው ግን የማይቀረውን የእርጅና ፊት ቢደቀንስ ? አያድርስ፤ ይሰውረን ነው መቼም! ከወደቻይና እንዲህ የሚልዜና ተሰምቷል። የ30 አመቱ ዩአን የሰማንያ አመት አዛውንት ፊት ይዞ መኖር ጀምሯል ይለናል ኦዲት ሴንትራል ድረገፅ ። በቻይና ችንግቂንግ መኖርያውን አርጎ በግንባታ ስራ ላይ በማናጀርነት ተሰማርቶ የሚገኘው ዩአን ገና በለጋ ዕድሜው በ30 አመቱ የ80 አመት አዛውንት ያስመሰለው በሽታ በውል የታወቀ ነገር የለውም።

ከበሽታው ሚፈውሰውን ፍለጋ ዘመናዊም ባህላዊም ደጅ ቢረግጥም ስለበሽታው አንዳች መፈወሻ መንገድ ይህ ነው የሚልው ግን አላገኘም። የዩአን መልክ በአንድ ጀምበር የተቀየረ ባይሆንም ዩአን ስለበሽታው ሲናገር እስከ 20 አመቱ የለጋነት መልኩን ይዞ እንደኖረ እንሰማለን። ከዚህ በኋላ ነበር ዩአን በፊቱ ላይ መስመሮችና በሰውነቱ ላይ እባጭ ማየት የጀመረው ። ዩአን መጀመርያ ነገሩን ከስራ እና ከውጥረት ጋር እያይዞት ቀለል አርጎት የነበረ ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን መስመሮቹ እየጎሉ ሲመጡ አንዳች እንዳለ መጠርጠር የጀመረው። ክዚህ በኋላ ለ9 አመታት ፈውስ ፍለጋ በየፈዋሹ ደጅ ቢመላለስም መፍትሄውን ይሄ ነው ሊለው የቻለ አንዳች አባ ፈውስ ሊያገኝ አልቻለም ።

የዩአን ያለድሜው ያረጀ ፊት ህይወቱን በበዙ መልኩ እያመሰቃቀለበት ይገኛል። በመታወቂያው ያለው ፎቶውና አሁን የያዘው መልኩ ፈፅሞ አይገናኙም ፤ እናም ህጋዊ ማስረጃዎቹ በሙሉ ከመልኩ ጋር ተጣርሰውበታል።

“ ከባለቤቴ ጋር በመንገድ ስንሄድ ሰዎች በግርምት ነው የሚያዩን” የምትለው የዩአን ባለቤት አንዳንዶች ደፍረው ጠጋ ብለው “ ወጣት ሆነሽ ከዚ ሽማግሌ ጋር ምን ትሰርያለሽ ” የሚሏትም እንዳልጠፉ ትናገራለች ። ምንም እንኳን ባሏ ምንነቱ ባልታወቀ እና መድሀኒት ባልተገኘለት ህመም ወጣት ሆኖ ሳለ የሸመገለ ቢመስልም አሁንም ከልቧ እንደምትወደው ትናገራለች። (ድንቅ ፍቅር!)

የዩአን በሽታ ገና ምንነቱ እየተጣራ ቢሆንም ታድያ ሌሎችም በመሰል ህመም የተጠቁ ሰዎች በነዩአን መንደር እና አጎራባች ቦታዎች ታይተዋል። የዩአን ታናሽ ወንድምም ገና በ25 አመቱ በመሰል ህመም ተጠቂ ሲሆን ሌሎች ሁለት የመንደሩ ሰዎችም በተመሳሳይ በበሽታው መያዛቸው ተሰምቷል። ከዚህም በመነሳት ይህ ህመም በዘር እንደማይተላለፍ ተዘግቧል።

ይህ እንግዳ በሽታ ታውቆ መድሀኒት እስኪገኝለት ገና በወጣትነቱ የአዛውንት መልክ መያዝ ግድ የሆነበት ዩአን “ እባካችሁ መላ የምታውቁ እርዱኝ ! ” እያለ ነው። ዩአን “ የችግሬን ስር መሰረት ምን እንደሆነ የሚነግረኝ እና የምፈወስበትን መንገድ የሚጠቁመኝ የአዋቂ ሰው ያለ!!” ሲል ተማፅኗል።

እኔም ፈጣሪ ምህረቱን ይላክለት ዘንድ እየተመኘሁ የዛሬውን የአጃዒብ ወሬዬን በዚሁ አበቃሁ። ቸር ይግጠመን

ቅንድል
DIGITAL MAGAZINE
TELEGRAM
@KENDEL
FACEBOOK
@KENDEL



# ”በስሜት መለዋወጥ ተሰቃየሁ!”



(fraolmesfin4@gmail.com)

በዚ ወር በተደጋጋሚ ስለ ስሜት መለዋወጥ ጥያቄ ከደረሰኝ በውሃላ በዚ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትሆን ዘንድ ይህችን ፅሑፍ ፃፍኩ ። በዚ ፅሑፍ የ ባይፖላርን ምንነት ፣ የባይፖላር የስሜት መለዋወጥ ችግሮች ምልክቶቹ ፣ ባይፖላር የስሜት ዲሶርደርን የሚያመጡ ምክንያቶችን እና ሕክምናውን እንዳስሳለን ። መልካም ንባብ ።

## ባይፖላር የስሜት መለዋወጥ ምንድን ነዉ?

ባይፖላር የስሜት መለዋወጥ ማኒክ ዲፕረሲቭ በሽታ በመባል ይጠራ የነበረው አንዱ የዲፕረሲቭ በሽታ ዓይነት ነው። ባይቦላር ዲስኦርደር ያለባቸው ሰዎች ስሜታቸው በጣም ይለዋወጣል። የመንፈስ መጨነቅ እና የሀዘን ስሜት ከዚያም ደሞ በጣም የደስታና የመፈንጠዝ ስሜት ይሰማቸዋል።

ባይቦላር የስሜት መለዋወጥ አንድ ፐርሰንት የሚሆነውን ሕዝብ ያጠቃዋል። 200 ከሚሆነው ህዝብ አንዱ ደግሞ በዚሁ ዲሳኦርደር በጽኑ ይታመማል። አስቀድሞ ችግሩን ማወቅና ጥሩ ህክምና ቶሎ ማድረግ ባይፖላር የስሜት መለዋወጥ ያለባቸው ሰዎች የወደፊት ኑሮአቸውን በደህንነት ለመጠበቅ ጠቃሚ ነው። ጥሩ ህክምና ካገኙ እራሳቸውን ችለው የተሟላ ህይወት ሊኖሩ ይችላሉ።

## የባይፖላር የስሜት መለዋወጥ ችግሮች ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

## ዲፕሬሽን (DEPRESSION)

ዲፕሬሽን ባይፖላር ዲስኦርደር ላለባቸው ሰዎች ለስሜታቸው መረበሽ ዋንኛው ምክንያት ሲሆን በሚከተለው ሁኔታ ይገለጻል

- ከዚህ በፊት ያስደስታቸው የነበረውን ነገር ለማድረግ ፍላጎት ማጣትና መቆጠብ፡
- በሐዘን መዋጥ
- ከጓደኞች መነጠልና ከማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች መራቅ
- እራስን ጣል ጣል ማድረግ፡ ለምሳሌ ወደ ገብያ አለመሄድና ሰውነትን አለመታጠብ
- የምግብ ፍላጎት መለዋወጥና የእንቅልፍ መስተጓጎል
- የሃሳብ መበተን፤ ከፍተኛ የድካም ስሜት፤ መጸጸትና ዋጋ የሌለኝ ሰው ነኝ ብሎ ማሰብ
- የተሳሳቱ የመወንጀል ሃሳቦችን ማሰብና ስለ ሌሎች ሰዎች መጸጸት፡

ጎጂ የሆነ አልኮልና እጽ መውሰድ ብዙውን ጊዜ ከዲፕሬሽን ምልክቶች ጋር በአንድ ላይ ይከሰታል። ይህም የሚሰጠውን ሕክምና ስለሚያዛባው አልኮልና ሌሎች እጾችን ከመውሰድ መቆጠብ በጣም ጠቃሚ ነው።

ዲፕሬሽን ያለባቸው ሰዎች እራሳቸውን የመግደሉ አደጋ ከፍተኛ ነው። *ስለዲፕሬሽን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ ቅንድል መፅሔት ቅፅ 2 "በ 2030 የዓለማችን ሶስተኛው ገዳይ በሽታ" በሚል ርዕስ ስለ ድብታ የተዘጋጀውን ጽሑፍ ያንብቡ።*

## ማንያ (MANIA)

ማንያ የሚለው ቃል እጅግ ጥልቅ የሆነ የደስታ ስሜትንና ከመጠን በላይ መወራጨትን የሚገልጽ ነው። ባይፖላር ዲስኦርደር ያለባቸው ጥቂት ሰዎች የማንያ ድርጊቶችን ሲያሳዩ ዲፕረሲቭ የሚያስከትለውን ድርጊቶች ግን አያሳዩም። የማንያ በሽታ የሚከተሉትን የተለምዶ ምልክቶች በተለያየ ደረጃ ያሳያል።

· የደስታ ስሜት፣ ግለሰቡ ከፍ ያለ የደስታ ስሜት እና የተሟላ ኃይል ይኖረዋል። ይህ ስሜት ብዙውን ጊዜ ከዓለም በላይ መሆንና ከሁሉም ልቆ መታየት የሚለውን ለመግለፅ ነው።

· የኃይል መጨመር እና ከመጠን በላይ መፈንጠዝ፤
· ለመተኛት ያለው ፍላጎት ይቀንሳል፤
· በቀላሉ መቆጣት- አንዳንድ ጊዜ የሚያመጣቸውን ተጨባጭ ያልሆኑ ሃሳቦቹን ከማይቀበሉና ከማይስማሙ ሰዎች ጋር መጋጨትና መበሳጨት።
· ፈጥኖ ማሰብና መናገር- ሃሳቡ ከተለመደው ጊዜ በጣም ይፈጥናል፡ ይህም ግለሰቡ ቶሎ ቶሎ እንዲናገርና ከአንዱ ሃሳብ ወደሌላው ነጥብ እንዲዘል ያደርገዋል፡
· ግዴለሽነት- ይህ ሊሆን የሚችለው ግለሰቡ የሚያደርገው ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ማሰብ ካለመቻል የሚመጣ ነው፣ ለምሳሌ ከሚገባው በላይ ወጪ አድርጎ የማያስፈልጉ ነገሮችን መግዛት።
· ግዙፍ የሆነ እቅድና እምነቶች- ማንያ ያለባቸው ሰዎች እራሳቸውን አግዝፈው የመመልከት ፀባያቸው የተለመደ ነው ።

ለምሳሌ፣ በእውቀት የበሰሉ ጸጋ ያላቸው፣ ወይም ንጉስ የሆኑ፣ የፊልም ኮከብ ተዋናይ ወይም ጠቅላይ ሚንስትር የሆኑ ይመስላቸዋል። ብዙውን ጊዜ የሳይማኖት እምነታቸው የጸና ይሆናል ወይም እራሳቸውን የሳይማኖት መሪ አድርገው ያቀርባሉ።
· ስለራስ አለማወቅ- ማንያ ያለባቸው ሰዎች ሃሳባቸውንና ድርጊታቸውን ሌሎች ሰዎች ትክክል እንዳልሆነ፤ ግዴለሽነትና መሰረተ ቢስ እንደሆነ አድርገው እንደሚቆጥሩት የሚያውቁት ቢሆንም ቅሉ እነሱ ግን ድርጊታቸው ስህተት ነው ብለው አያምኑም።
· ማንያ መኖሩ የሚታወቀው ምልክቶቹ ለአንድ ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ የታዩ ከሆነ ነው። ሃይፖማንያ መለስተኛና ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ነው

## ጤናማ የሆነው ስሜት

የማንያና የዲፕሬሽን ምልክቶችንና ድርጊቶችን የሚያሳዩ ብዙ ሰዎች በየጣልቃውም ጤናማ ስሜትን ያሳያሉ። የቤትም ሆነ መደበኛ ስራቸውን በመከወን ጤናማ ህይወታቸውን ሊመሩ ይችላሉ። ስሜታቸው ከመጠን በላይ ዝቅና ከፍ ሲልና በኑሮአቸው ውስጥ ጣልቃ ሲገባ ብቻ ነው የአዕምሮ በሽታ ምርመራና ሕክምና ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው።.

## ባይፖላር የስሜት ዲሶርደርን የሚያመጣው ምንድን ነው?

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በዚህ የአዕምሮ በሽታ የመያዝ እድላቸው እኩል ነው። ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ሰዎች በሃያዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ሲሆኑ ቢሆንም ከዚያ በፊት ወይም ከዚያ በኋላ ሊመጣ ይችላል። ባይፖላር የስሜት ዲስኦርደር በተለያዩ ነገሮች መዳመር- ለምሳሌ በዘር (ጄኔቲክስ)፣ በሰውነት ንጥረ ነገሮች (ባዮኬሚስትሪ) እና በአካባቢ ሁኔታ ሊመጣ ይችላል።

## በዘር (ጄኔቲክስ)

የቅርብ ዝምድና ያላቸውን ለምሳሌ አንድ አይነት መንታዎችንና ወላጆቻቸው ባይፖላር የስሜት ዲስኦርደር ባላቸው የማደጎ ልጆች ላይ የተደረገው ጥናት በሽታው በዘር እንደሚተላለፍ አበክሮ አመልክቷል። ወላጆቻቸው በበሽታው የተያዙ ልጆች በበሽታው የመያዝ አደጋ የተጋለጡ ናቸው።
የሰውነት ንጥረ ነገሮች (ባዮኬሚካል)
እንደ ማንያ ያለ ዲፕሬሽን የሚመጣው በአንጎላችን ውስጥ ያለው የኬሚካል ምጥን መዛባት አንዱ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። በመድሃኒት መታከም ይቻላል።

## ስትሬስ (የኑሮ ጫና)

ሁልጊዜ ባይሆንም እስትሬስ የበሽታውን ምልክቶች በመቀስቀስ ከፊል ድርሻ ሊኖረው ይችላል። በሽታው እራሱም የኑሮ ጫናዎችን ሊያስከትል ይችላል (ለምሳሌ፣ መፋታት ወይም የንግድ ኪሳራ ሲመጣ) ታዲያ ይሄ በበሽታው ሊሳበብ ይችላል።

## ያለው ሕክምና ምንድን ነው?

ለባይፖላር የስሜት ዲስኦርደር ወጤታማ የሆነ ጥሩ ሕክምና አለ። ስለ ሕመሙ ትምህርት መውሰድና ቅድመ ምልክቶችን ለይቶ ማወቅ እና የመከላከያ እርምጃዎችን እንዴት መውሰድ እንደሚቻል ማወቅ ጠቃሚ ነው። በዚህ ረገድ በተለይ የቅርብ ሰው የሚሰጠው ድጋፍ እጅግ አጋዥ ነው።

ሕመሙ ዲፕሬስ በሚያደርግበት (በሚያስጨንቅበት) ጊዜ የአንታይ-ዲፕሬሳንት ህክምና ማግኘት ከዲፕሬሽን ስሜት ያወጣል፣ ጤናማ የሆነውን የመኝታ ሰዓትና የምግብ ፍላጎትን ያስተካክላል፣ መረበሽንም ይቀንሳል። አንታይ-ዲፕሬሳንት መድሃኒቶች ሱስ የሚያሲዙ አይደሉም። በአንጎል ውስጥ ያሉትን የኒዎ-ትርንስሚተሮች መጠን ቀስ በቀስ ያስተካክላሉ፣ አጥጋቢ ውጤት ለማግኘት ከአንድ እስከ አራት ሳምንት ይወስዳል።

አጣዳፊ ወይም ጽኑ የሆነ ማንያ ሲከሰት ብዙ የተለያዩ መድሃኒቶች ይታዘዛሉ። ከፊሉ መድሃኒት ግለሰቡን ከመረበሽ ሲያወጡት ሌሎቹ መድሃኒቶች ደግሞ የማንያክ ስሜቱን ያረጋጋሉ።

ሌሎች መድሃኒቶችም የመከላከል ድርሻ ሲኖራቸው የስሜት መለዋወጥን ለመቆጣጠርና የዲፕሬሲቭና የማንያክ ምዕራፎች በጭራሽ እንዳይከሰቱና ብዙ ጊዜም እንዳይመጣ ያደርጋሉ።

በተደጋጋሚ ህመሙ የሚከሰት ከሆነ የረጅም ጊዜ ህክምና ማግኘት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የኑሮ ሁኔታን መለወጥ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ እና ጎጂ የሆኑ አልኮልና ዕጽ መቀነስ፣ ሌሎችም ህመሙን ከሚቀሰቅሱ መቆጠብ ህመምተኞች እንዲድኑ ለማድረግ ያግዛል።

የስነ-ልቦና (ሳይኮሎጂካል) ምክሮችን መስጠት የህክምናው አንዱ ጠቃሚ ክፍል ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ህክምናዎች ለምሳሌ ኮግንቲቭ ቢሄቪየራል ቴራፒ (CBT) መውሰድ፣ ለህመሙ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትንአንዳንድ የአስተሳሰብ ሁኔታዎችን፣ ጸባይን እና እምነቶችን ለመቀየር የታለመ ነው።

ከሰዎች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት ህክምና (ኢንተርፐርሰናል ቴራፒ)- ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ጠቃሚ ከሆኑ ሰዎች ጋር ግንኙነታቸውን በአዲስ መንገድ እንዲቀይሱ ያስተምራል። ሰዎች በማኒክ ምዕራፍ ውስጥ ሲገቡ፡ ህክምና ያስፈልጋችኋል ብሎ ለማሳመን በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

የህመሙ ምልክቶች ከተባባሱ ግለሰቡን ሆስፒታል ማስገባት አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ብዙ ሰዎች በጭራሽ ሆስፒታል ገብተው አያውቁም፡ እዛው ማህቡብ ውስጥ ሆነው በተመላላሽ የህክምና አገልግሎት እያገኙ ሊቆዩ ይችላሉ። ባይፖላር የስሜት ዲስኦርደር ያለባቸው ሰዎች ተገቢ የህክማናና የእርዳት አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ እንደማንኛውም ሰው የተሟላና ጤናማ ኑር ሊመሩ ይችላሉ። የባይፖላር የስሜት ዲስኦርደር ያለባቸው ሰዎች ቤተሰቦችና ጓደኞች ብዙውን ጊዜ ግራ ሊጋቡና ጫናው ይሰማቸዋል። እርዳታ ማድረግና ስለሆኔታው መማር፣ እንዲሁም ማህበረሰቡ ስለ ህመሙ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ለህክምናው አንዱ ጠቃሚ ክፍል ነው።

ቸር እንሰምብት

በ ዞስ ካለስ




አስትሮሎጂ እጅግ ጥንታዊ ነገር ግን የተረሳ ሳይንስ ነው። ከነፍስ እስከ ዩኒቨርስ፣ ሚለው መፅሐፍ ላይ፣ እንደተገለፀው፣ የሰው ልጅ የተመዘገበ ታሪክ ከተጀመረበት ግዜ አንስቶ የነበረ ጥንታዊ የጥናት ዘርፍ ሲሆን፣ በሱሜርያን ስልጣኔ የአስትሮሎጂ ፅሁፎች የተገኙት፣ ከክርስቶስ ልደት 2500 አመት በፊት ነው። በህንድ ደግሞ ከዛም በላይ ጥንታዊ መሆኑን ሲገለፅ፣ "ሪግ ቬዳ " (የሂንዱይዝም ቅዱስ መፃፍ) ላይ የክዋክብት ስብስቦች አሉ፣ እነዛ የክዋክብት ስብስቦች (constellation) አሁን በሳይንቲስቶች ሲመረመሩ የታዩት ከ9500 አመት በፊት ነበር ። ስለዚህም መፅፉም የተፃፈው ከዚያ ግዜ በፊት ሆኖ ተገኝቷል፣ በዚህ አማካኝነትም፣ ዋና ዋናዎቹ የአስትሮሎጂ ህጎች የተገኙት ከህንድ ነው ልንል እንችላለን። ከዚ ጋር በተያያዘም ሂሳብ የመጣውም ከአስትሮሎጂ የተነሳ ነው ተብሎ ሲገመት፣ ኮኮብ ለመቁጠር እንዲመቻቻው የተፈጠረ ስሌት መሆኑን ይጠቁማሉ።

››› ሱሜሪያኖች ከ250 ሜትር በላይ የሆነ ግዙፍ ማማዎችን ገንብተው ማማው ላይ በመሆን ኮኮቦችን በጥልቅ መመርመር ያዙ፣ ከዚያ ምርምር በመነሳትም ሱሜሪያኖች የሰው ልጅና ከዋክብት ምን ያህል ጥልቅ ግንኙነት እንዳላቸው፣ እንደውም ምንጮቻችን እነሱ እንደሆኑ ደረሱበት። እንዲሁም ምንም አይነት በሽታ ወይም ጥፋት ቢከሰት ክስተቱ ከክዋክብት ጋር ይገናኛል ብለው ያስቡ ነበር።

አሁን ታድያ ለሳይንስ ክብር ምስጋና ይግባውና እነዚህን ሀሳቦች የሚረጋግጡልን ጠንካራ ድንቅ መነሻዎችን አሳይቶናል።

››› በ 1920 የሩሲያ ተወላጁ "አሌክሳንደር ቼዜቭስኪ" እንዲህ አለ
"በፀሀይ የላይኛው ቅርፊት ላይ በየግዜው 'ሶላር ፍሌር' የተባሉ ከፍተኛ ፍንዳታዎች ይከሰታሉ፣ ነገር ግን በአስራ አንድ አመት አንዴ የሚከሰተው ፍንዳታ እጅግ በጣም ሀይለኛ ነው፣ ይህ ክስተት የፀሀይ ኡደት( solar cycle) ይባላል።"

ታድያ በቼዜቭስኪ ጥናት መሰረት እነዚህ ከፍተኛ ፍንዳታዎች በፀሀይ ላይ በተከሰቱ ቁጥር ምድር ላይ ደግሞ ጦርነት አመፆች ይከሰታሉ። እንደ ጥናቱ ከሆነ፣ በ700 አመት የአለም ታሪክ ውስጥ ፍንዳታው በፀሀይ ለይ በየአስራ አንድ አመቱ በተከሰተ ቁጥር ምድር ላይ የሆነ ከባድ ጥፋት ወይም ጦርነት ይከሰታል፣ ተከስቷልም። ምንም እንኳን የቼዜቭስኪ ምርምር እውነት እና በመረጃ የተደገፈ ቢሆንም፣ በዛን ግዜ ከነበረው የማርክስ ርዕዮታ አለም ጋር ስለተጋጨ የራሺያ ባለስልጣናት ወደ ሳይቤሪያ እስር ቤት ወርውረውታል።

›››› ለምሳሌ የፀሀይ ግርዶሽ ከመከሰቱ ከ24 ሰዓት ጀምሮ አእዋፋት መዘመር ያቆማሉ፣ በግርዶሽ ሰአትም መላው ጫካ በዝምታ ይዋጣል። አእዋፋት በሙሉ በፍርሀትና በጭንቀት ውስጥ ይሆናሉ፣ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ከዛፎች ላይ ወርደው መሬት ላይ በቡድን በቡድን ሆነው ይቀመጣሉ፣ ራሳቸውንም የመከላከያ ዘዴ መሆኑ ነው። አስጋራሚው ነገር ደግሞ በመጮህና በመንጫጫት የሚታወቁት ጦጣዎች በግርዶሽ ሰዓት በፍፁም ፀጥታ መዋጣቸው ነው። ምንም እንኳ ቼዜቭስኪ ይህንን ነገር ለማብራራት ቢሞክርም የዚህ አውነታ መነሻው ጥንት የሱሜሪያን ስልጣኔ መሆኑ ነው።

›››› በመቀጠልም ፓራክሊስስ የተባለ ስዊዘርላንዳዊ የህክምና ዶክተር ተጨማሪ ግኝቶችን አገኘ፣ ግኝቱ እጅግ አስገራሚና የህክምና ሳይንስን ትልቅ እርምጃ የሚያራምድ ሲሆን ነገር ግን እስካሁንም ይህን ግኝት ሳይንቲስቶች አምነው መቀበል አልፈለጉም። አስትሮሎጂ የተረሳና ችላ የተባለ ሰይንስ ነው የምንለውም ለዛ ነው። የፓራክሊሰስ ግኝት እንደሚለው ከሆነ አንድ ሰው የሚታመመው ሰውየው ሲወለድ ሰማይ ላይ ከታዩት የክዋክብት ስብስቦች በሆነ መልኩ ሲረበሹ ወይም ሲበተኑ ነው ይላል። ለማንኛውም እሱ ጋር ለሚመጣ ህመመተኛ የተወለደበትን ወቅት አይቶ በደንብ ሳያጠና መድሀኒት አያዝለትም ነበር። አስጋራሚው ነገር ደግሞ የተወለዱበትን ግዜ አጥንቶ መድኃኒት የሰጣቸው በሽተኞች ወዲያው መዳናቸውና ለሌሎች ዶክተሮች ከባድና ግራ አጋቢ የሆነ ህመሞችን ሁሉ እሱ ከልደታቸው ወቅት አንፃር መርምሮ መፍትሄ መስጠቱ ነው። ይሁን እና አሁን ላይ የሱ ምርምሮችም ሆነ ግኝቶች ተረስተዋል። ነገር ግን አሁን ባላፉት ሃምሳና ስልሳ አመታት የአስትሮሎጂ ጥናት በድጋሜ እየተነሳሳ ነው፣ በ1950 ዓ.ም "ኮስሚክ ኬሚስትሪ" የሚባል ሰይንስ ተወለደ። ፈጣሪውም "ጆርጅ ጂያርጂ" የተባለ ከክፈለ ዘመኑ ትልልቅ ሰዎች መሀል የሚመደብ ሰይንቲስት ሲሆን፣ ስለ ክዋክብትም ብዙ አስደናቂ ጥናትን አድርጓል።

›››› ታማቶ የተባለ ጃፓናዊ ዶክተር ደግሞ ሌላ እጅግ አስደናቂ ግኝት አገኘ። የሴቶች ደም ከወንዶች ደም ለየት የሚያደርገው አንድ ባህርይ አለው። ይህም የወር አበባ በሚያዩ ሰዓት ወይም በእርግዝናቸው ሰዓት የሴቶች ደም በመጠኑ መቅጠኑ ነው። የወንዶች ግን ሁሌም ያው ነው። ታድያ አስገራሚው ነገር ከላይ የገለፅነው አይነት የአቶሚክ ፍንዳታ በፀሀይ ላይ በአስራ አንድ አመት አንዴ ሲፈነዳ የወንዶችም ደም ይቀጥናል ። ይህ አስገራሚ ጉዳይ ነው፣ ፀሀይ ላይ የተፈጠረ ረብሻ ደማችን ላይ ይህን አይነት ለውጥ መስከሰት እንዴት ቻለ??

›››› ውቅያኖሶች ላይ ማዕበል የሚነሳው በጨረቃና በፀሀይ ስበት እንደሆነ ሳይንስ ካረጋገጠው ቆይቷል። ግን ልብ ያላልነው ነገር በውቅያኖስ ውስጥ የሚገኘው የውሃና የጨው መጠን በሰው ልጅ አካላት ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚገኝ ነው። የኛ ምድር 70% ውሃ የተሞላ ሲሆን በተመሳሳይ የኛ ሰውነትም 70% ውሃ ነው። ታድያ የውቅያኖስ ውሃ በጨረቃና በፀሀይ ስበት የሚረበሽ ከሆነ የኛ ሰውነትስ እንዴት ተፅኖ አያርፍበትም?

›››› ከጥንትም ጀምሮ ሰዎች አስትሮሎጂ ተራ አፈ-ታሪክ እንደሆነ ብሎም ከሰይጣን ጋር የተያያዘ ክፉ ስራ ብለው ይፈርጁታል። ነገር ግን አሁን አሁን ታላቅ ሳይንሳዊ ድጋፍ አግኝቷል። እንግዲህ ሳይንስ ማለት በአንድ ነገር መንስኤና ውጤት ላይ የሚመራመር ጥናታዊ ውጤት ነው። አስትሮሎጂ የሚለው እዚህ ምድር ላይ የተፈጠረ የትኛውም ክስታት መንስኤ አልባ አይደለም ነው። የፊታችን ከኋላችን ጋር ሊለያይ አይችልም። እንደውም ጥብቅ ትስስር አላቸው፣ ነገ የሚከሰተው የትኛውም ነገር ዛሬ ትንሽ ደበቅ ባለ መልኩ እየተከሰተ ነው ይለናል።



»» ለምሳሌ ዲጃ ቩ (deja vu) የሚባል ክስተትን መቼም ሁላችንም እናውቀዋለን። አንድን ክስተት አንድአንዴ ቀድመን ያየነው የሚመስለን አጋጣሚ አለ። አንድአንዴ ደግሞ ሰዎች በህልማቸው የተመለከቱትን ነገር በእውን ሲከሰት ሰምተንም ገጥሞንም እናውቃለን። ታድያ ይህ ህልም ወይም የዲጃ ቩ ክስተት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ያልኖርነውን ማየት ቻልን? አስትሮሎጂ እንደሚለን ወደፊት ማለት የኛ ቸልተኛነት መገለጫ ነው እንጂ ልብ ካልነው ቀድመን ልናየውም የምንቸለው ክስተት ነው። የአሁኑን መስኮት መክፈት ከቻልን ወደፊትን በግልፅ ማየት እንችላለን። ጥበቡን አለማወቃችን፣ ወይም ቸልተኝነታችን ነው ወደፊትን እንዳናይ የከለከለን።

»» ፖፑሌሽን ሪፈረንስ ቢሮ ( population references bureau) የተባለ ተቋም ባጠናው ጥናት መሰረት እስካሁን በአለም ውስጥ 108 ቢሊዮን ህዝቦች ኖረዋል ተብሎ ይገመታል። አሁን ያለነው ሳንቆጠር ማለት ነው። ታድያ ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ የአንዱ የጣት አሻራ ከአንዳኛው ጋር በፍፁም ተመሰስሎ አያቅም። ወደፊትም ከሚወለዱት ጋር አይመሳሰልም። ከአንድ እንቁላል የተፀነሱ መንትዮች እራሱ የጣት አሻራቸው

ይለያያል። ታድያ
ተፈጥሮ የጣት አሻራን አይነት ምንም የማይጠቅም ነገር ለእያንዳንዱ ሰው ልዩ አድርጋ ከሰጠች ህይወትና ነፍስን ልዩና ብቸኛ ለማድረግ ምን ያቅታታል? እርግጥ ሳይንስ ቀሰስተኛ ነው። ከብዙ ሙከራና ምርምር በኃላ ነው ወደ መደምደሚያ የሚደርሰው።

አስትሮሎጂ የወደፊቱን የሚመረምር ነው። ሰይንስ ደግሞ የኋለው ላይ ነው፣ ስለወደፊትም ሲገምት በፊት ከተፈጠሩ ክስተቶች በመነሳት ብቻ ነው። አስትሮሎጂ የሚያጠናው ደግሞ ዛሬ የተከሰቱ ነገሮች ወደፊት የሚያስከትሉትን ውጤት ነው። ነገር ግን ሳይንስ ይህን ርቀት ለማጥበብ እየተጋ ይገኛል። ሳይንስ የሰው ልጅ ሲፀነስ የራሱን ግላዊ ማንነት ይዞ እንደሆነ የተረዳው አሁን በቅርብ ነው፤ በጄኔቲክስ (genetics) ጥናት።

አሁን አሁን ሳይንቲስቶች ሌላው ቀርቶ የአይናችን ቀለም የፀጉራችን ቀለም፣ የሰውነታችን ቁመት የአስተሳሰባችን ደረጃ ሁሉ በዘራችን ውስጥ ተነድፎ እንደተቀመጠ አምነዋል። እሱ ብቻ ሳይሆን በአሁን ሰዓት የዕፅዋቶችን ዘሮችን በመመርመር የነሱን ንድፍ ማወቅ ችለዋል። ታድያ ከዚህ ቀጥለው የሰው ልጅ ንድፍ መመርመር ከቻሉ ሰይንስና አስትሮሎጂ ተዋሀዱ ማለት አይደል?

››› አስትሮሎጂ እንደሚለው ከሆነ በሆነ ጥበብ ሁሉን ማወቅ ሲቻል ወደፊት የሚባለው ነገር አይኖርም። ምክንያቱም አንዴ ያንን ዘር መመርመር ከቻልን የህወታችን ንድፍ በመልክ በመልክ ተቀምጦ እናገኘዋለን ማለት ነው። ምናልባትም በጥቂት አመታት ውስጥ ሳንይንስ ይህን ዘር በጥልቁ መረዳት ችሎ የሰው ልጅችን እጣ መተንተን ይቻለው ይሆናል። ምክንያቱም አንዳንድ ተስፋ ሰጪ እርምጃዎች እየታዩ ስለሆነ። ለምሳሌ የሰውን ልጅ DNA በማጥናት ግለሰቡ በምን አይነት በሽታ ሊያዝ እንደሚችል፣ የእድሜ ገደቡ ምን ያህል እንደሆነና ሌሎች ነገሮችንም ማዋቅ ችለዋል። ከዛም በማለፍ አንድ ዘር ከእንቁላል ጋር ከመዋሀዱ በፊት DNA መርምረው ያለበትን ድክመትና ጉድለት በማጥራት የተሻለ ማንነት፣ ውበትና ረጅም እድሜ ያለው ሰው ለመፍጠር በሙከራ ላይ ናቸው።

››› ስለዚህ ዞዳይክንና የውልደት ሰንጠረዥ መመልከት ይህን ምስጢር ለመረዳት ከመሞከር የመጡ ናቸው። ስለዚህ አስትሮሎጂ ኮኮብ ቆጠራ ብቻ አይደለም። ኮኮቦችን መቁጠር አንዱ ክፍሉ ሆኖ እጅግ ጥልቅና ሰፊ ሰይንስ ነው፣ ስለ አስትሮሎጂ ትንተና አለም ላይ አሉ ከሚባሉ አጥኚዎች፣ ቀዳሚዎች እኛ ኢትዮጵያዉያን መሆናችን፣ አለም ሚያውቀው ሀቅ ነው፣ አሁንስ ምንስ አገደን? አሁንስ ምን ላይ ነን?

ቅንዲል
Digital Magazine
MobileApp
በቅርብ ቀን!



በ ሎዛ አድማሱ
(lozaad2017@gmail.com)

# ጥሊ

የአንተ የህይወት መርህ ፍቅር ከተባለ መቅሰፍት በተቻለ አቅም መራቅ ነው። ምክንያቱም ፍቅር ይሰብራል። እናትህ ለዚህ ማሳያ ነች። ከአባትህ ጋር ከተፋቱ ጀምሮ ስቃ እንኳ የምታውቅ አይመስልህም። የሰፈሩ ሰው ፍቺ ይበለው እንጂ ቤተሰባችሁ በሙሉ ግን በህግ እንዳልተጋቡ ያውቅ ነበር። እናም አባትህ በእምነት ብቻ ያቆማችሁትን ቤት ለመተው አንድ በአንድ እቃውን ሲያወጣ እናትህ ያለችውን መቼም አትረሳውም። ‹‹እኔ ነኝ ጥፋተኛ። የሆነ ነገር ጎድሎበት ነው።››

‹‹አንተ የኔ ልጅ ነህ፤ ልክ እንደእኔ ነህ።›› አለህ አባትህ በብዙ ጊዜህ ስትጎበኘው። አንተ ግን የእናትህ ልጅ ነህ። እናትህ ግን ስቃ አታውቅም። ምናልባት አንተ ስትመረቅ ትስቅ ይሆን( እንጃ። የአንተ መርህ ግን ፍቅር ከተባለ መቅሰፍት መራቅ ነው። ማርከሻ የሌለው መርዝ ነዋ።

ቅንዝንዝ አድርጎህ በሰው ልከህ አሳደህ ተሳደህ የተኛኃቸው ብዙ ሴቶች አሉ። ብዙዎቹ ቆንጆ ናቸው። ትላልቅ ጡቶች አሏቸው። ክብ ክብ መቀመጫ። ሲስቁ አፋቸውን በመጠኑ ብቻ የሚከፍቱ። ሲጎርሱ የከንፈር ቀለማቸው እንዳይበላሽ የሚጠነቀቁ። ይዘኃቸው ስትገባ በቅናት ያላየህ ወንድ አለ( በእንከን አልባ ሰውነታቸው እየተርመሰመስህ የኪራይ መኝታችሁ ላይ ገነት አይተህ ተመልሰኃል። ከእኒያ ሴቶች የመጀመሪያ ስም ውጪ ለምን ምንም አልጠየቅኃቸውም( ግን ሁሌም ስትጨርስ ገላህን ሙልጭ አድርገህ ትታጠባለህ። ለምን( ጠዋት ለጓደኞችህ ‹አሪፍ ምሽት› እንዳሳለፍህ ስትነግራቸው ለምን ጠዋት የተሰማህን ባዶነት ደበቅኃቸው ስትጠጣ ዝምታ ታበዛለህ። እንደውም ስቅስቅ ብለህ ትከሻህ እስኪረግፍ ያለቀስኸው ጓደኛህን ቴዎድሮስን ከልጅቷ ጋር ሸኝተህ ወደቤት ስትገባ ባለው ውስጥ ለውስጥ ነው። አንተ ሞቅታ ውስጥ ነበርህ። ቴዎድሮስ ግን ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ነበር። ለምን እንዳለቀስህ አልገባህም። በህይወትህ የሚያስለቅስ ምንም ሀዘን የለም። ግን ደግሞ ደርሶ የሚያፍነከንክ ደስታም የለም። እንደኩሬ የረጋ ነበር። ህይወትህ።

ከዚያ አንድ ቀን እሷን አዋራኃት። ‹‹ጠቢብ ደስ የሚል ስም ነው›› አለችህ። አንድ አመት ሙሉ ጊቢ ውስጥ ያየኃት ልጅ እንደአዲስ ሰው ብርቅ የሆነችብህ ግን የዚያን እለት አይደለም። እንደአጋጣሚ ተገናኝታችሁ ለራስህ ብቻ የያዝኃቸውን ታሪኮች ስትነግራት ነው። የዚያን እለት ልብህ ቀለል አለልህ። አውርተኃት ስትጨርስና ‹‹ይሄን ሁሉ ጊዜ ሳንተዋወቅ›› ስትልህ ቀጥሎ በምን ሰበብ እንደምታገኛት እያሰብህ ነበር። ስትስቅ ሙሉ ፊቷ ይፈካል። ብዙ ጊዜ ስለምትስቅ ፊቷ ብዙ ጊዜ የፈካ ነው። ስትስቅ ሳቋ እያሳቀህ ስትስቅ፤ ሳቅህ እያሳቃት ስትስቅ፤ ሳቋ እያሳቀህ ስትስቅ…

ሌላ ቀን አገኘኃት። ደግሞ ሌላ። ደግሞ ሌላ። ደግሞ ሌላ። ትናንሽ ወንበሮች ያሉበት ቤት ብዙ ቀን ጁስ ጠጣችሁ። አስተናጋጇ ኮስታራ የነበረችበት ቤት ችፕስና ማኪያቶ። እሷ እየሳቀች ‹‹ሁለቱም ይጣፍጣሉ ግን አንድ ላይ አይሄዱም›› አለች። ሁለታችሁም የምትወዱት ቤት ብዙ ነገር በላችሁ። ብዙ ነገር ጠጣችሁ።ብዙ ነገር አወራችሁ።



ስታወራላት ጸጉርህን አሻሸችህ። በጣቶቿ በኩል አርካሽ መርዝ የገባ ይመስል በውስጥህ የቋጠርካቸው እስሮች ሁሉ ሲፈቱ ተሰማህ። የሚያሳድዱህ መንፈሶች ሁሉ የሸሹ መሰለህ። እንዲህ በጣቶቿ እያሸችህ ዝንተአለም ቢያልፍ ብለህ ተመኘህ። ደስስስስ አለህ።

እኔ መውደድ አልፈራም ስትልህ ፈራህላት። ተይ ፍሪ እንጂ ፈሪ ለእናቱ ነው ስትላት ስቃ አቀፈችህ። ያንን ሹራብ ስንት ቀን ለበስኸው( የቆንጆ ሴቶችን ላቦት የተጠየፈ ገላህ የእሷን መንካት ወዶት ማረፉ ለምን አስደነገጠህ(

አንድ ቀን ግን ረሳኃት። በቃ ረሳኃት። ሳታስባት ዝም ብለህ ሌላ ሌላ እያሰብህ ተኛህ። ስልክህ ቀሰቀሰህ። እርግማን። እሷ ነች። ምን ሆና ነው በሌሊት( ሀሳብ ገባህ። ‹‹ገባህ( በሰላም ነው( ተኝተህ ነው( የምትወደውን ገዝቼ እየጠበቅሁህ ነበር።›› ድምጽዋ ቀዝቅዟል። ረስተኃት ነው። ማታ አገኝሻለሁ፤ እናወራለን ያልኃትን ረስተኸው ነው። ገረመህ። የዚያን ሌሊት እንቅልፍ አልወሰደህም። ‹‹አንተ የኔ ልጅ ነህ፤ ልክ እንደእኔ ነህ።›› ያሉህ አባትህ ትዝ አለህ። አስተዋይ ሽማግሌ አልህ በሆድህ።

የጸሀይ ፊቷ መዳመን ምክንያት መሆንን ፈራህ። ድምጽዋ ለዘላለም ሲቀዘቅዝ። እንደእናትህ መሳቅ ስታቆም። አንተ የአባትህ ልጅ ነህ። እሷ ግን እናትህ መሆን የለባትም።ዘጋኃት።

እሷ፡ ኮስታራዋ ሴትዮ ጋር ችፕስና ማኪያቶ ልጋብዝህ(
አንተ፡ አይመቸኝም።
እሷ፡ ምን አባህ ልትሰራ ነው( እሺ ቀረብ ያለ ቦታ ሻይ እንጠጣ
አንተ፡ አይመቸኝም፤ ብዙ ስራ አለኝ። ሲመቸኝ
እሷ፡ ምን ሆነኃል(
አንተ፡ ምን ሆንሁ(
እሷ፡ እኔ እኮ ይቅርታ አድርጌልኃለሁ፤ ለራስህ ይቅርታ አድርግ
አንተ፡ ምንድን ነው የምታወሪው( ይቅርታ የሚያስባብል ምን ግንኙነት አለን(

ዝም አለች። የዚያን እለት ማታ ሞቅ እንኳ ሳይልህ ትከሻህ እየተርገፈገፈ አለቀስህ። የአንተ የህይወት መርህ ፍቅር ከተባለ መቅሰፍት በተቻለ አቅም መራቅ ነው። ምክንያቱም ፍቅር ይሰብራል።

300 ሺህ
ሰዎችን ይድረሱ!

ምርትና አገልግሎትዎን በቅንድል ዲጂታል መፅሔት ያስተዋውቁ። በገቢው ግማሽ የበጎ አድራጎት ስራን ይደግፉ።

**ለበለጠ መረጃ**

(+251) 0912178520

(+251) 0920019699

**ይደውሉ!**

በ ዞስ ካለስ

# ሀሳብን ወደ ፅህፍ እና ድምፅ መቀየር የሚችል የቴክኖሎጂ ውጤት ይፋ ሆነ

የካንሰር፣ የስኳርና ትላልቅ አደጋዎች በሰው አካል ላይ በትልቅ ደረጃ ጉዳት ሚያደርሱ ከሆነ፣ ልሳንን በመዝጋት የሰዎችን የመናገር ፀጋ በማጥፋት እንዳይናገሩ ያደርጋሉ። በዚህም ሚፈልጉትን ቃላት እንዳይገልፁ ከሚያደርጉ በሽታዎች መካከል ዋንኞቹ ናቸው። አሁን በቅርብ የመጣው ቴክኖሎጂ ይሄንን ችግር በብቃትም ሆነ በፍጥነት መቅረፍ ችሏል፣ ይሄም በአዕምሯችን ምናስበውን ሐሳብ ወደ ቃላትና ፊደል መተርጎም አስችሏል። በዚህም ምክንያት የጠፉና የረሳናቸውን ቃላት ወደ ዋላ ለመመለስ ሚደረገውን ጥረት አጋዥ ከማድረግ አንፃር ብዙ እርምጃዎች እንደሚኖሩት በምርምሩ ባለሞያዎች ተገልፇል። ሀሳብን ቀጥታ ከአዕምሮ በመውሰድ ወደ ቃላት ሚቀይር ቴክኖሎጂ ለመስራት ብዙ ሙከራ ማድረጋቸውን የገለፁት ተመራማሪዎቹ፣ የምርምሩ መሪ ኤድዋርድ ቻንግ (ኒውሮሰርጂን በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሳንፍራሲስኮ) አሁን የተገኘው ግኝት አመርቂ ውጤት መሆኑን ገልፀዋል።

እስከ ቅርብ ግዜ የነበረው ቴክኖሎጂ መልክታቸውን በአግባቡ ማስተላለፍ የማይችሉትን ሰዎች፣ በአይን ቆባቸው፣ በአይናቸው ወይም በግንባራቸው በመታገዝ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ መልክታቸውን ሲያስተላልፉ የነበሩ እንደሆነ ሲገልፁ፣ ለምሳሌ እውቁ ፊዚስት ፕሮፌሰር ስቴቨን ሀውኪንግ መልክቱን ሚያስተላልፈው ጉንጮቹ ጋ ባሉት ጡንቻዎች በመጠቀም አጠገቡ ባለው የመተርጎሚያ ኮምፒተር እርዳታ አማካኝነት ሲሆን፣ እሱ በሚያሳየው መጠቆሚያ ምልክት አማካኝነት፣ መናገር የፈለገውን ወደ ቃላት ይለውጥለታል፣ ቃላቶቹም፣ አረፍተ ነገር በመሆን ትርጉም አዘል፣ ፍቺዎችን ይሰጣል። የሞተር ኒውሮን ህመም ተጠቂ የሆኑት እኚ ፕሮፌሰር ፣ ማንኛውንም የሰውነት እንቅስቃሴ እንደፈለጉ ለማድረግ የተገደበ እንቅስቃሴ ስለሚያደርጉ፣ መናገርም ሆነ መንቀሳቀስ አይችሉም፣





የኢንቴል ኮምፒውተር ትብብር ባለሞያዎች ምስጋና ይግባቸውና፣ ከስቴቨን ሀውኪንግ ጋር በቅርበት በመሆን ወደ ሁለት አመት የፈጀ ኮምፒተር በንግግር በኩል ያለውን ክፍተት ሞልተውለታል።

በወቅቱ የነበርውን ግዜያዊ ችግር በተወሰነ መልኩ በመፍታት ብዙ ምርምሮችና መፃፎችን እንዲፅፍ ቢረዳቸውም፣ ሚጠቀምበት አካሄድ ግን በጣም ቀርፋፋ ከመሆኑ የተነሳ፣ ሀሳቦቹን ትርጉም ወደ አለው አረፍተ ነገር ለመለወጥ በደቂቃ ውስጥ ከ 1 እስከ 10 ቃላቶችን ብቻ ነበር መሰብሰብ ሚችለው። የሰው ልጅ በደቂቃ ውስጥ ከ120 እስከ 150 ቃላት፣ መናገር ይችላል። ሰዎች ሀሳባቸውን በፍጥነት ለመናገርም ሆነ ለመግለፅ ፍላጎት አላቸው፣ ስቴቨን ሀውኪንግ ሚጠቀምበት ኮምፒተር ግን ይሄን ፍላጎታቸውን ማሳካት አያስችለውም ነበር። ፍጥነት ያላውን መልክት ማስተላለፍ በሚፈልጉት ላይም እንቅፋት በመፍጠር ስልቹና ብስጩ እንደሚየደርጋቸው አያጠያይቅም።

ከዚጋ በተያያዘም፣ ቻንግና ባልደረቦቹ የቃላቶቹን ፍጥነት ጭምር በማሻሻል፣ በአዕምሯችን ውስጥ ያለውን የድምፅ ትርጉም ሚሰጠውን አካል በመረዳት፣ የከንፈር፣ የምላስ፣ የመንጋጭላና የድምፅ ሳጥን፣ ክትትል በማድረግ ራሱን ችሎ በተዘጋጀ ኤሌክትሮድ አማካኝነት ቀጥታ የአዕምሮ የድምፅ መተርጎሚያ የሰውነት ክፍል ውስጥ በማስቀመጥ፣ መናገር በማይችሉና ሀሳባቸውን መግለፅ በሚከብዳቸው ሰዎች በቀላሉ ወደ ትርጉም አዘል ቃላትና ድምፅ በመለወጥ ይረዳቸዋል ብለዋል።

ኤሎክትሮዶቹ መናገር የተፈለገውን ሀሳብ በመቃረም፣ በተገቢው መልኩ ትርጉም በመስጠት የተሳካ ውጤት ማምጣት ቢችሉም፣ መጀመሪየ ላይ እንደ እንከን ከታዩት ሙከራዎች ውስጥ አንዱ "Shh" ሚለውን "ship" ብሎ ሲተረጉም፣ B ሚለውን "bob" ብሎ ተርጉሟል፣ ይሁንና ቴክኖሎጂው ራሱን በራሱ የማሻሻልና አዳዲስ ቃላትን የመልመድ ብቃት ስላለው፣ ችግሩን ራሱ መቅረፍ ያስችለዋል። ከ70% በላይ ሚሆኑ ትርጉሞችን በተሳካ መልኩ ትክክለኛ ቃላትንም አምጥቷል፣ ያልተሳኩትም ቢሆን ከትክክለኛ አረፍተ ነገር የራቁ አልነበሩም፣ የተወሳሰቡ ትርጉም የቃላት ሀረግ ላይ አላመጡም።

ለምሳሌ ትክክለኛ አረፍተ ነገሩ " እዛ ሌቦች አስራ ሰባት ቀለበቶችን ሰረቁ ሚል ከሆነ የተገኘው ስተት፣ አስረሶስት ሌቦች፣ አስረ ሶስት ቀለበቶችን ሰርቀዋል ሚል ነበር፣ እንደዚ አይነት አስተኛ ስተቶችን ከስንት አንዴ ቢገኙም በቀላሉ መፍተት ሚቻሉና ክትትል ላይ ያሉ መሆናቸው ነግረውናል።

አሁን ላይ በትክክል መናገር በሚችሉት ላይ ብቻ የተሞከረው ይሄ ቴክኖሎጂ፣ ለተመራማሪዎቹ ትልቅ ችግር የሆነባቸው በቂ በጎ ፍቃደኞችን ማግኘት አለመቻላቸው መሆኑን አቶ ቻንግ ተናግረዋል፣ አምስት ሚሆኑ በጎ ፍቃደኞች ላይ ሙከራ ሲካሄድ፣ እያንዳንዳቸው አንድ ወይም ሁለት የኤሌክትሮዶች መተርጎሚያ እቃዎች፣ ፓዶችና በሺ ሚቆጠሩ ትናንሽ ኤሌክትሮዶች የተገጠመላቸው ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው በሺህ ሚሆኑ ቃላትን በሀሳብ ደረጃ ሲናገሩ፣ የከንፈር፣ የምላስ፣ የመንጋጭላና የማንቁርት ክትትል ከተደረገባቸው ቧላ፣ የተሰካ ውጤት አስገኝተዋል፣ በደቂቃ ውስጥም እስከ 150 ቃላትን መተርጎም ሚችል እንደሆነ ተነግሯል።

ከዚ ጋ በተያያዘም ጆሽ ቻርተር (ኒውሮሎጂስት) አሁን የተሰራው ነገር ድንቅ መሆኑን ተናግረው፣ ከዚ በተሻለ መንገድ ብዙ ምርምሮችን ማድረግ እንዳለበት አሳስበዋል፣ ከምርምሩ አስተባባሪ ከሆኑት ቻንግ ጋርም በትብብር እየሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል። አቶ ቻንግም አሁን ላይ የቃላት ጥራትና የማሽኑን ተደራሽነት የማረጋገጥ ስራ ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ይፋ አድርገዋል።





በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ
( lijyoha@gmail.com )

#እልፍገፆች

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ቤተሰቦች!ቢያነቧቸው ይማሩበታል ይዝናኑበታል ብዬ ያሰብኳቸውን መፅሀፍት በዚህ አምድ ስር እጋብዛለሁ።መልካም የንባብ ጊዜን ተመኘሁ!




እነሆ ጀግና በስብሀት ገብረእግዚአብሄር ተፅፎ ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1998 ዓ.ም ለአንባቢያን የደረሰ እና በዓለም ላይ ያሉ የታዋቂ ሰዎችን አጭር የህይወት ታሪክ የያዘ መፅሀፍ ነው።

ማሀተማ ጋንዲ ከሱባኤያቸው ሲወጡ ህዝብን ለአመፅ በመቀስቀስ ክስ ተይዘው ለፍርድ ቀረቡ።እምነት ክህደት ሲጠየቁም እንዲህ የሚል መልስ ሰጡ"እኔ እዚህ የቀረብኩት ለህግ ወንጀል የሆነ ለኔ ግን ከፈተኛ ተግባር የሆነ ድርጊት በመፈፀሜ ለጣስኩት ህግ ከሁሉ ከፍተኛ የሆነውን ቅጣት ለመቀበል ነው"(ከመፀሀፉ የተወሰደ)

መጸሀፉ 20 የአለማችንና የሀገራችንን ታላላቅ ሰዎች አጭር የህይወት ታሪክ ሲይዝ በ171 ገጾች ተሰናድቶ በ120 ብር ለገበያ ቀርቧል።መፀሀፉ እስከ 2010 ባለው ጊዜ ውስጥ 10 ጊዜ ለህትመት በቅቷል።
ደራሲው እምስ፣ስድስት፣ሰባት፧ሌቱም አይነጋልኝ፧ትኩሳት እና ሌሎችንም ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል ።




በ በአሉ ግርማ ተፅፎ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1975 ዓ.ም. በማንኩሳ አሳታሚ በኩል ለህትመት የበቃው ይህ መፅሀፍ 1967 ዓመተምህረት ላይ ያለውን ዘመን በልብወለዳዊ ዘዬ ቃኝቶ በሚጥም ቃላት በዓሉ አቅርቦልናል።መፅሐፉ በ323 ገፆች ተሰናድቶ በ71 ብር ለገቀያ ቀርቧል።




በ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የተፃፈውና በጥር ወር 2010ዓ.ም. ለተደራሲያን የቀረበ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣እንዲሁም ግለሰባዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ መፅሀፍ ነው።

"ገበያ ሲያመች የማይሰራ ኢ-ሞራላዊ ሥራ የለም።ገበያ ሲያመች ሀገር ይሸጣል፣ጎሊና ይሸጣል፣መሬት ይሸጣል፣ቅርስ ይሸጣል፣ስም ይሸጣል፣ባህል ይሸጣል፣ፍትህ ይሸጣል፣እናት አባት ይሸጣሉ፣እምነት ይሸጣል፣ገበያ ካመቸ ህሊናን ይሸጡታል።ምን የማይሸጥ አለ።መመዘኛው ትክክል ነው አይደለም፣ሞራላዊ ነው አይደለም፣እውነት ነው አይደለም፣ሕጋዊ ነው አይደለም የሚለው ሳይሆን ያዋጣል ወይንስ አያዋጣም የሚለው ብቻ ነው።እንደነዚህ አይነት ሰዎች የሚሞቱለት አቋም፣ሐሳብ፣ርዕዮተ አለም፣መስመር፤እምነት፤ማንነት፣ራዕይ የላቸውም።(ከመፅሀፉ የተቀነጨበ)

በ 4 ምዕራፎችና በ 28 ርዕሶች የተሰናዳ ሲሆን 210 ገፆችን ይዞ በ85 ብር ለገበያ ቀርቧል።




"Tower In The Sky"በሚል ርዕስ በህይወት ተፈራ በእንግሊዝኛ የተፃፈውና "ማማ በሰማይ"ተብሎ በጌታነህ አንተነህ ወደ አማርኛ የተመለሰው ይህ መፀሀፍ በ2007 ዓ.ም. ለንባብ በቅቷል።

ማማ በሰማይ የፍቅር ታሪክ ነው።የአብዮትም፣የተስፋም፣የህልምም፣የአመፃም፣የሽብርም፣የመተማመንም፣የመከዳዳትም፣የሰቆቃም፣ራስን በራስ የመለወጥም፣የድል አድራጊነትም የነዚህ ሁሉ ሰብዓዊ ረቂቅ ባህርያት ታሪክ ነው።መፀሀፉ፣ደም የጠማው ወታደራዊ ጁንታ ባቀጣጠለው ታይቶ የማይታወቅ የጅምላ ጭፍጨፋ ሀገሪቱ በሞላ በተወራጨችበት፣ተሰምቶ በማይታወቅ ቁጥር ህዝብ በተለይ ወጣቱ እንደ ቅጠል የረገፈበት የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ወቅት ቅልብጭ ያለ ስዕል ነው።

በታሪክ ውስጥ ብቅ ብለው ከጠፉት እጅግ ጨቃኝ አንባገነን ስርዓቶች አንዱ በሆነው ላይ በመነሳት እና በቁርጠኝነት በመጋፈጥ ለእኩልነት፣ለነፃነት፣ለማህበራዊ ፍትህ እና ለሰባዊ ክብር የታገሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታሪክ ነው። መፅሐፉ በ386 ገፆች ተሰናድቶ በ152 ብር ለገበያ ቀርቧል።

የዚህ እትም የመፀሀፍት ግብዛዎቼ ይህን ይመስላሉ በሌላ እትም እስክንገናኝ መልካም የንባብ ጊዜን ተመኘሁ!

"ሰላም በምድራችን ላይ ይስፈን"


e
Eyou pictures
WEDDING
MODELING PHOTO
BIRTHDAY
Address:-Bole. /
medehanialem ,South Gate Plaza ,
2nd floor / office No 205
DIAL
0912416606
0947317608